ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ረቡዕ

82ኛ ዓመት ቁጥር 158 የካቲት 8 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# የውጭ ግንኙነትን ለማጠናከር ከአገራት መሪዎች ጋር የዲፕሎማሲ ሥራዎች ይሠራሉ

## - 42ኛው የአፍሪካ ኅብረት የሥራ አስፈጻሚ ምክር ቤት ጉባዔ ዛሬ ይጀመራል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት ለማጠናከር ከዋናው ጉባዔ ጎን ለጎን ከተለያዩ አገራት መሪዎች ጋር ጠቃሚ ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎች እንደሚሠሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ 42ኛው የአፍሪካ ኅብረት የሥራ አስፈጻሚ ምክር ቤት ጉባዔ ዛሬ ይጀመራል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር 36ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባዔንና 42ኛው የአፍሪካ ኅብረት የሥራ አስፈጻሚ ምክር ቤት ስብሰባን አስመልክቶ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ የዘንድሮው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባዔ ‹‹የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ትግበራን ማፋጠን›› በሚል መሪ ሃሳብ ይካሄዳል፡፡

በ36ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባዔ ከ51 አገሮች የተውጣጡ የልዑካን ቡድኖች ይገኛሉ፡፡ የዘንድሮ ጉባኤም የተለምዶ ዓመታዊ ምልልስ ሳይሆን አባል አገራት በስብሰባው ላይ በባለብዙ ወገንና በሁለትዮሽ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ዙሪያ በመወያየት የብሔራዊ ጥቅማቸውን


የውጭ ግንኙነትን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ - በዮሐይ ገጊሜ

አምባሳደር መለስ ዓለም



አቶ ሀጂ ኢብሳ

# ሁሉም ተቋማት የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት የግዥ ሥርዓትን እንዲጠቀሙ ባለሥልጣኑ አሳሰበ

- ሥርዓቱ እስከ 25 በመቶ የሚሆነውን የመንግሥት በጀት መቆጠብ ያስችላል


ገጽ 4


# በክልሉ ከ730 ሺህ በላይ የመማሪያ መጻሕፍት ህትመት እየተከናወነ ነው

## - 140 ሺህ የሚጠጉ መጻሕፍት በሚቀጥሉት 10 ቀናት ይሰራጫሉ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ከ186 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ተማሪዎች በየትምህርት ዓይነቱ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ የተዘጋጁ 730 ሺህ 633 መጻሕፍት ህትመት እየተከናወነ እንደሚገኝ የአፋር ክልል ትምህርት ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአፋር ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አብዱ ሀሰን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በዕውቀትና ሥነምግባር የታነጸ ትውልድ ለመቅረጽ በክልሉ መንግሥት ወጪ የመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት ህትመት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በዚህም ከአንደኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ለሚገኙ ከ186 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ተማሪዎች የሚሆን 730 ሺህ 633 የመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት ህትመት እየተከናወነ ነው፡፡ የሰባተኛ እና ስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች 139 ሺህ 770 መጻሕፍት ህትመት ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል ብለዋል፡፡

ህትመታቸው የተጠናቀቀው 139 ሺህ 770 የመማሪያና


በክልሉ ከ730 ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




አቶ አብዱ ሀሰን

# የቃሊቲ ቱሉ ዲምቱ መንገድ በተያዘው ዓመት ለትራፊክ ክፍት ይሆናል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የቃሊቲ ቱሉ ዲምቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በዚህ ዓመት ተመርቆ ለትራፊክ ክፍት እንደሚሆን የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡ የመንገዱ ግንባታ 60 በመቶ መድረሱ ተገልጿል፡፡

የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ እያሱ ሰለሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሁን ላይ ግንባታ ሥራው ላይ የነበሩት ችግሮች ተቀርፈው የተቀሩት ሥራዎች በፍጥነት እየተከናወኑ ነው፡፡በመሆኑም መንገዱ በዚህ ዓመት ተመርቆ ለትራፊክ ክፍት ይሆናል ብለዋል፡፡


የቃሊቲ ቱሉ ዲምቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## በአዲስ አበባ የሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ እየተፋጠነ ነው




ገጽ 3



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ

ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia



ኢብ
የሴቶች ንፅህና መጠበቂያ
0911113801 0911176500

አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
Adama Steel Factory
Our Products




Tel: 0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80
0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06

# የአፍሪካ የመሪዎች ጉባዔ በሰላም እንዲጠናቀቅ በቂ ዝግጅት ተደርጓል




**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የአፍሪካ የመሪዎች ጉባዔ ያለምንም የጸጥታ ችግር እንዲጠናቀቅ በቂ ዝግጅት ተደርጎ ወደ ሥራ መገባቱን የአዲስ አበባ ፖሊስ አስታውቋል፡፡

የአዲስ አበባ ፖሊስ ሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ምክትል ኮማንደር ማርቆስ ታደሰ እንደገለጹት፤ የአፍሪካ የመሪዎች ጉባዔ በሠላም እንዲጠናቀቅ ከጸጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይል ጋር ዕቅድ በማዘጋጀት አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሠረት የጸጥታ አካላት እንግዶችን በምን መልኩ ማጀብ እና መጠበቅ እንዳለባቸው አስፈላጊውን የተግባር ልምምድ ማድረጋቸውን አንስተዋል፡፡

ጉባዔው እስከሚጠናቀቅ ድረስ የእንግዶችን ሠላም እና ደኅንነት ለማስጠበቅ በሁሉም ዘርፍ አስተማማኝ ዝግጅት ተደርጎ ወደ ሥራ መገባቱን ተናግረዋል፡፡

እንግዶች ከሚያርፉባቸው ሆቴሎችና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ተቋማት ጋርም በቅርበት እና በትብብር መሥራት የሚያስችል ትሥሥር መፈጠሩን ዳይሬክተሩ ገልጸዋል፡፡

ማኅበረሰቡም በተለመደው ኢትዮጵያዊ ጨዋነት በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ ለእንግዶች ቅድሚያ በመስጠት እና ተገቢውን ክብር በማሳየት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ ጠይቀዋል፡፡

በተለይም እንግዶች በተለያዩ አካባቢዎች በሚንቀሳቀሱበት ወቅት መንገዶች ሊዘጉ ስለሚችሉ ተሽከርካሪዎች እና እግረኞች በትዕግስት እንዲጠብቁም ነው የጠየቁት፡፡

የአፍሪካ መሪዎች ጉባዔ የኢትዮጵያን ገጽታ የሚያጎላ ነው ያሉት ምክትል ኮማንደሩ፤ የመዲናዋ ነዋሪዎች ጉባዔው በሠላም እንዲጠናቀቅ የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ጥሪ ማቅረባቸውን ኤፍቢሲ ዘግቧል።

ነዋሪዎች በየትኛውም ሁኔታ አጠራጣሪ ነገር ሲመለከቱም በአዲስ አበባ ፖሊስ ስልክ ቁጥር 011 111 0111 ወይም በ991 በመደወል ጥቆማ መስጠት ይችላሉም ነው ያሉት።

# አፍሪካ ኒዩክሌርን በመጠቀም የኃይል አማራጮቿን ማስፋት አለባት

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- አፍሪካ የኒዩክሌር ኃይልን መጠቀም የኃይል ምንጭ አማራጮቿን በማስፋፋት ኢኮኖሚዋን በዘላቂነት ማሳደግ እንደሚኖርባት የዘርፉ ምሁራን ገለጹ፡፡

የዘርፉ ምሁራን እንደሚሉት አፍሪካ ሰፊ የማዕድን ክምችት ያላት በመሆኑ ተመጣጣኝና ንፁህ ኃይል ለማግኘት እንዲሁም በኢኮኖሚው፣ በሕክምናው፣ በግብርናውና በተለያዩ ዘርፎች ተጠቃሚ እንድትሆን የኒዩክሌር ኃይል የምታመነጭበትን አሠራር መዘርጋት አለባት፡፡

የኬንያው ታዳሽ ኢነርጂ ማህበር ዋና ሥራ አስፈጻሚ አንድሪው አማዲ (ዶ/ር) እንዳሉት፡- የኒዩክሌር ኃይል የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት በጣም አነስተኛ ወጪ የሚጠይቅና አፍሪካም የዩራኒየም ክምችት ስላላት ብሎም ቴክኖሎጂው ትንሽ ዩራኒየም ብቻ የሚጠቀም በመሆኑ ተጠቃሚ ያደርጋታል፡፡ አገራት እየተፈተኑበት ያለውን የኃይል አቅርቦት እጥረት ለመቅረፍም የኒዩክሌር ኃይልን ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡

ከአየር ንብረት ለውጥ ነፃ መሆኑ፤ ከፍተኛ ኃይል በትንሽ ግብአትና በአጭር ጊዜ ማመንጨት መቻሉ የኒዩክሌር ኃይል ከሌሎች የታዳሽ ኃይል ምንጮች ተመራጭ የሚያደርገው መሆኑን ያብራራሉ ፡፡

ኒዩክሌር ከሌሎች የኃይል ምንጮች ጋር ሲወዳደር እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው የሚሉት ምሁሩ፤ በዓለም ላይ ያሉ አብዛኛዎቹ የበለጸጉ አገራት የኃይል ምንጫቸው በኒዩክሌር ኃይል ልማት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የአፍሪካ የኢነርጂ ደህንነትን ለማረጋገጥ ከበለጸጉ አገራት ትምህርት መውሰድ አለባት ይላሉ።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ የኒዩክሌር ኃይል ቴክኖሎጂን በማስተዋወቅ የራሷን አቅም ማጎልበት እንደሚኖርባትም ዋና ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል፡፡

የዓለምአቀፉ ኢነርጂ ማህበር አባል የሆኑት አቤል ዲዲየር ቴላ የኢነርጂ ልማት የአፍሪካውያን ዋነኛ ትኩረት መሆን አለበት፤ በአሁኑ ወቅት በአፍሪካ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የኤሌክትሪክ ኃይል እጦት ችግር ላይ ናቸው። የአህጉሪቱ ሁለንተናዊ እድገትም በኃይል እጥረት እየተፈተነ ነው። የተለያዩ የኃይል ምንጭ አማራጮችን መፈለግ እንደ ቅንጦት መታየት የለበትም፤ እናም ኒዩክሌርም እንደ አማራጭ የኃይል ምንጭ ወስዶ መሥራት ያስፈልጋል ነው ያሉት፡፡

ዓለምአቀፉ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ ከአፍሪካ ኅብረት ጋር የካንሰር በሽታ መከላከል በሚያስችሉ ሥራዎች ዙሪያ በጋራ መሥራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነት የዛሬ ዓመት በአዲስ አበባ መፈራረማቸው ይታወሳል።

የኢትዮጵያ ኒዩክሌር ሳይንስ ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ እምሻው ዳምጠው እንደተናገሩት፤ ኒዩክሌር ኢነርጂ ታዳሽ ኃይል ከሚባሉት ውስጥ ይመደባል፡፡ በአገራችን የኒዩክሌር ኃይል ቴክኖሎጂ ብዙም ባይታወቅም ኢትዮጵያም ከዘርፉ በሰፊው የምትጠቀምበት ዕድል እንዳለ ያስረዳሉ።

የኒዩክሌር ኃይል በህክምናው፣ በግብርናው፣ በኢንዱስትሪውና በሌሎች ዘርፎችም ሁለተናዊ ዕድገት ከፍተኛ ጥቅም ስላለው የኒዩክሌር ሳይንስ በሁለተኛ ደረጃና በዩኒቨርሲቲ ትምህርት የሚሰጥበትን ዕድል ቢፈጠር ወደፊት አገራችን በታዳሽ ኃይል ተጠቃሚ ትሆናለች ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የበለፀጉ አገራት በኒዩክሌር ቴክኖሎጂ የደረሱበትን የእድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ስለኒዩክሌር ቴክኖሎጂ ሁሉም ተገንዝቦ በየዘርፉ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ደግሞ ለአገሪቷ የኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል ብለዋል፡፡



# የሴቶችን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በትኩረት እየተሠራ ነው

**በሪሁ አረጋ**

አዲስ አበባ፡- የሴቶችን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡

የብልፅግና ፓርቲ ሴቶች ሊግ ጽሕፈት ቤት አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ወይዘሮ አሰለፈች ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የሴቶች ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግና ለማረጋገጥ እየተሠራ ነው፡፡

ሊጉ ሴቶች የፖለቲካ አቅማቸውን የሚያጎለብቱበት መድረክ በማዘጋጀት ሴቶች የአመራር ብቃታቸውን እንዲያዳብሩ ብሎም ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ በትኩረት እየሠራ ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ በተለይ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ላይ ተሰማርተው ራሳቸውንና አገራቸውን እንዲለውጡ ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸውን አክለው ገልጸዋል፡፡ በዚህም በከተማ ግብርና የተሰማሩ ሴቶች ብቻ ሲታይ አስደናቂ ውጤት ማስመዝገባቸውን እንደምሳሌ አንስተዋል፡፡

የሴቶች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት እየተሻሻለ መምጣቱን የጠቆሙት ኃላፊዋ፤ በፖለቲካው እና ኢኮኖሚው ዘርፍ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡና ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ የተለያዩ ስልጠናዎችን በመቅረፅ የተለያዩ ትምህርቶችንም እንዲያገኙ ሊጉ ባለፉት ስድስት ወራት በርካታ ሥራዎችን ሠርቷል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሴቶችን ወደ አመራርነት ለማምጣት እና ውሳኔ ሰጪ እንዲሆኑ ሊጉ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ እንደሚገኝም አክለው ገልፀዋል፡፡

የሴቶች ውሳኔ ሰጪነት በአመራርነት ብቻ የሚወሰን አይደለም ያሉት ወይዘሮ አሰለፈች፤ በተለያዩ ዘርፎች ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ ከከፍተኛው የሥልጣን ደረጃ ጀምሮ እስከታችኛው ባሉት የአመራርነት ደረጃ ሥራዎች የሴቶችን ቁጥር ከፍ ለማድረግም ሊጉ የበኩሉን ድርሻ በተገቢው ተወጥቷል ብለዋል፡፡

የሴቶችን የአመራርነት ቁጥር በዘንድሮው ዓመት 30 በመቶ ማምጣት እንዲቻል አቅጣጫና መመሪያ ተቀርፆ እየተሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

በትምህርታቸውና በሥራቸው ግንባር ቀደም የሆኑ ሴቶች እየተለዩም ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች ጋር በመተባበር አጫጭር የተግባቦትና የክህሎት እንዲሁም የእቅድና አፈፃፀም ስልጠናዎች እንዲወስዱም እየተደረገ ይገኛል ሲሉ ገልፀዋል፡፡

በኢኮኖሚ ራሷን የቻለች ሴት ከቤት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ደረጃዎች መወሰን የምትችል ሲሆን ይህ እንዲሆንም የመጀመሪያ ሥራው ከምትሠራውና ከምታገኘው መቆጠብ ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ የተቆጠበው ገንዘብም ለተለያየ የኢንቨስትመንት አማራጮችንና የሥራ ዕድሎችን እንዲጠቀሙ እንደሚደረግ አንስተዋል፡፡

የሥራው ትልቁ ተግዳሮትም በሁለቱም ወገን ያለ የአመለካከት ችግር መሆኑን ወይዘሮ አሰለፈች ገልፀው፤ በወንዶች ዘንድ ሴቶች አይችሉም የሚለው የቆየ አስተሳሰብ እስካሁን ባለመቀረፉና ሴቶችም እራሳቸውን እንደልማድ ይዘውት የመጡት ከኃላፊነት የመሸሽና ከተጠቃሚነት የመራቅ ዝንባሌ እስካሁንም ያልተሻገርነው ችግር ነው ብለዋል፡፡

ሊጉም በተቻለ መጠን ለሚስተዋሉ ዘርፈ ብዙ የአመለካከት ችግሮች እየተከታተለ ለመቅረፍና ሴቶችም በራሳቸው ተነሳሽነት የተፈጠሩትን ዕድሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየሠራ ነውም ብለዋል፡፡

# የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የወጣቶችን ስብዕና በአዎንታዊ አስተሳሰብ እየገነባ ነው

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለአገር ግንባታ ከሚያበረክተው አስተዋፅዖ ባሻገር የወጣቶችን ስብዕና በአዎንታዊ አስተሳሰብ እየገነባ ነው ሲል የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጣቶች ብሔራዊ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ማስፋፊያ መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ዐቢይ ኃይለመለኮት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ለአገር ግንባታ ከሚያበረክተው አስተዋፅዖ በተጨማሪ የወጣቶችን ስብዕና በአዎንታዊ አስተሳሰብ እንዲገነባ ጉልህ ሚና እየተጫወተ ነው፡፡

በዚህ መንገድ ያለፉ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተሻለ ስብዕና ኖሮአቸው ስለሰውና ስለአገር እንዲያስቡ እንደሚያስችላቸው የተናገሩት አቶ ዐቢይ፤ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚከናወኑ ተግባራት ለአገር ከሚሰጡት ጠቀሜታ አንፃር በገንዘብ ቢተመን መንግሥት ሊያወጣ የሚችለውን ከፍተኛ ወጪ ማዳን እየተቻለ እንደሆነ ገልፀዋል።

ወጣቶች የበጎ አድራጎት ሥራዎችን በሚያከናውኑበት ጊዜ ዕውቀትና ባህል እንዲሁም በአንድነትና በፍቅር አብሮ የመኖር ዕሴቶችን



አቶ ዐቢይ ኃይለመለኮት

ከማህበረሰቡ እንደሚያገኙ ገልጸው፤ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ መከሰቱ ምንም እንኳን መጥፎ አጋጣሚ ቢሆንም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ያለው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ እንደመጣ ተናግረዋል። ሕዝቡ የበጎ ፍቃድ ሥራዎች ላይ ያለው ተሳትፎ የሚበረታታ እንደሆነና እያደገ መጥቶ ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንደደረሰ አቶ ዐቢይ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ዐቢይ ገለፃ፤ ባሁኑ ወቅት ዜጎች የእረፍት ጊዜያቸውን ጠብቀው በተለያየ ቡድኖች በመደራጀት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ላይ እየተሳተፉ ነው፡፡ ለአብነትም የስፖርት ቡድን ደጋፊዎች፣ በተለያየ መንፈስና አውድ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በአንድ ላይ በመሆን የደም ልገሳና የአካባቢ ፅዳት ዘመቻዎችን እያደረጉ ነው፡፡ መሰል ተግባራት ባህል ለማድረግ አጠናክሮ መሥራት ይገባል።

የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሕዝብና ሕዝብ ተቀራርቦ እንዲሠራም ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳለው ገልጸው፤ ወሰን የለሽ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሥራ በተከናወነበት ወቅት ወጣቶች በሁሉም ክልሎች ተዘዋውረው የሠሩትን እንደ አብነት አንስተዋል፡፡

የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን በተደራጀ መልኩ ለማስቀጠል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተለያዩ የበጎ ፍቃድ ኅብረቶችን በመፍጠር በሌላው የዓለም ክፍል ላይ ያሉትን መልካም ተግባራት ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት የተለያዩ የአሠራር ሥርዓቶችን ለመዘርጋት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ፖሊሲ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝም አቶ ዐቢይ ጠቁመዋል።



አቶ አዲስ አረጋይ

# በአዲስ አበባ የሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ እየተፋጠነ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ እየተከናወኑ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ እየተፋጠነ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

በጽሕፈት ቤቱ የኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ አዲስ አረጋይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ፕሮጀክት ግንባታ 57 በመቶ ደርሷል። በተመሳሳይም የትራንስፖርት ቢሮ ተቋማት ሕንፃ ግንባታ ፕሮጀክት 53 በመቶ የተጠናቀቀ ሲሆን የየካ ሁለት የመኪና ማቆሚያ ፕሮጀክት ግንባታ ደግሞ 38 በመቶ ደርሷል።

አቶ አዲስ አያይዘውም፤ የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ክላስተር ግንባታ ፕሮጀክቶች ግንባታም የተጀመረ ሲሆን የግብርና ምርቶች መሸጫ ማዕከላት ግንባታ ፕሮጀክት ደግሞ 23 በመቶ ደርሷል፡፡ በቅርቡ የተጀመረው የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ማስፋፊያ ግንባታም አምስት በመቶ ላይ ደርሷል፡፡

የሴቶች የተሀድሶና የመልሶ ማቋቋሚያ ግንባታ ፕሮጀክት እና የዓደዋ ዜሮ ኪሎ ሜትር ሙዚየም ግንባታ ፕሮጀክት ያሉበት ደረጃ በቅርቡ እንደሚገለጽም አቶ አዲስ ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ የአነስተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ክላስተር ግንባታ ፕሮጀክት፣ የግብርና ምርቶች መሸጫ ማዕከላት ግንባታ ፕሮጀክት፣ የዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ማስፋፊያ ግንባታ ፕሮጀክትና የሴቶች የተሀድሶና የመልሶ ማቋቋሚያ ግንባታ ፕሮጀክት በ2015 ዓመተ ምህረት የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ናቸው ያሉት አቶ አዲስ፤ በፕሮጀክቶቹ እስካሁን ከስምንት ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል ብለዋል።

ከነባር ፕሮጀክቶች መካከል እስካሁን አራት ፕሮጀክቶች ለአገልግሎት በቅተዋል ያሉት አቶ አዲስ፤ መስቀል አደባባይ የመኪና ማቆሚያና እስከ ማዘጋጃ ቤት የመንገድ ማስዋብ ሥራ፣ አብርሆት ቤተመጻሕፍት፣ የከንቲባ ጽሕፈት ቤት ስር ነቀል እድሳት እና አንድነት የመኪና ማቆሚያ ማስረከብ ተችሏል ብለዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ የአዲስ አበባ ሜጋ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት አዲስ የሥራ ባህልና የአሠራር መንገድን ቀይሶ በፕሮጀክቶች መዘግየት ሳቢያ ይደርስ የነበረውን ተጨማሪ የገንዘብና የጊዜ ብክነት ማስቀረት ችሏል።

በተጨማሪም ግንባታዎቹ ዘመን ተሻጋሪና በዚህ ትውልድ መታነጻቸው ታሪክ ጭምር በመሆኑ ትላልቅ ግንባታዎችን በተያዘላቸው በጀትና በተቆረጠላቸው የግንባታ ጊዜ አጠናቆ ወደ ታለመላቸው ሥራ የማስገባቱ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

ጽሕፈት ቤቱ እስከ 2017 ዓመተ ምህረት ድረስ ሃያ ትላልቅ የፕሮጀክት ግንባታዎችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ፣ ወጪ እና ጥራት እንዲጠናቀቁ በማድረግ፤ የግንባታ ቴክኖሎጂ ሽግግር ለማምጣት እየሠራ እንደሆነ ተናግረዋል።



# የሐሮማያ ሐይቅ አገግሞ የዓሣ ምርት መስጠት ጀመረ

ታደሰ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- ደርቆ የነበረው የሐሮማያ ሐይቅ በመልሶ ማልማት ሥራ በማገገሙ የዓሣ ምርት እየሰጠ እንደሚገኝ ተገለጸ፡፡

የሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ ተሳትፎና ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ይስሀቅ ዩሱፍ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራ በመሥራት በ2003 ዓ.ም ሙሉ በሙሉ ደርቆ የነበረው የሐሮማያ ሐይቅ ወደ ነበረበት ተፈጥሮዊ ይዘቱ እንዲመለስ ማድረግ ተችሏል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ በየዓመቱ 400 ሺህ ችግኞችን በመትከሉ የደረቀውን ሐይቅ መልሶ ወደ ነበረበት እንዲመለስ በማድረግ ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡

የሐይቁ ውሃ በመልሶ ማልማት ሥራ በማገገሙ ለአካባቢው ማህበረሰብ የዓሣ ምርት እየሰጠ እንደሚገኝና የአካባቢው ነዋሪ ወጣቶች ተደራጅተው የሥራ ዕድል ማግኘት እንደቻሉ ገልጸዋል፡፡

ከተለያዩ አካባቢዎች እየመጡ ሐይቁን ለሚጎበኙ የአገር ውስጥና የውጭ ቱሪስቶች ስምንት ጀልባዎች የሽርሽርና የጉብኝት አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙና ሐይቁ ወደ ነበረበት ተፈጥሮ መመለሱ የቱሪስት መስህብ ሆኖ የአካባቢው ማህበረሰብ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ አድርጎታል ብለዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲው የተሠራው የተፋሰስ ሥራ ሐይቁን ከመድረቅ መታደግ እንደቻለና የሐይቁን የውሃ መጠን በሰባት ሚሊዮን ሜትሪክ ኩብ ከፍ ማድረግ ተችሏል ሲሉም ዶክተር ይስሀቅ አብራርተዋል፡፡

ተቋሙ ሐይቁን ወደ ነበረበት እንዲመለስ ትኩረት ሰጥቶ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና የተፋሰስ ሥራ መሥራት በመቻሉ ሐይቁ መሻሻል እንዳሳየ እና በ1986 ዓ.ም ከነበረው የውሃ መጠን ጋር ሲነፃፀር 70 በመቶ የውሃ መጠን ጭማሪ አሳይቷል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በሐይቁ አካባቢ ያለውን የተጎዳ መሬት በተፋሰስ ሥራ በማልማትና የተለያዩ እፅዋቶችን በመትከል የአካባቢውን ማህበረሰብ በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ተጠቃሚ የማድረግ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

ተቋሙ የአካባቢውን ማህበረሰብ ከማገልገል በተጨማሪ በአገሪቱ እየታየ ያለውን የአየር ብክለት ለመቀነስ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

# ዩኒቨርሲቲው በቀጣዩ ዓመት የካንሰር ሕክምና ይጀምራል

**ታደሰ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የካንሰር ሕክምና ማዕከል በቀጣይ ዓመት ሙሉ በሙሉ የካንሰር በሽታ ሕክምና አገልግሎት እንደሚሰጥ ተገለጸ፡፡

የሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ ተሳትፎና ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ይስሀቅ ዩሱፍ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው በአካባቢው ለሚኖረው ማህበረሰብ በተለያዩ ዘርፎች አገልግሎት እየሰጠ ነው።በዚህም በመሠረተ ልማት፣ በትምህርት ጥራት፣ በጤናና በመሳሰሉ ዘርፎች ማህበረሰቡን ተጠቃሚ እያደረገ ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲው በጤናው መስክ በሪፈራል ሆስፒታሉ በዘርፉ ከባድ የሚባሉ የሕክምና ግልጋሎቶችን ለዜጎች አልፎ ተርፎም ከጅቡቲና ሶማሌ ላንድ ለሚመጡ ህሙማን አገልግሎት በመስጠት ማህበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣና ትልቅ ሚና እየተጫወተ ነው ብለዋል።

ተቋሙ የካንሰር ሕክምና ማዕከል ገንብቶ በዘንድሮው ዓመት የሕክምና የሙከራ ሥራ ማስጀመሩን የገለጹት ዶክተር ይስሀቅ፤ ማዕከሉ የሕክምና ሙከራ መጀመሩ ወደ ፊት የካንሰር በሽታ ሕክምናን ለአካባቢው ማህበረሰብ ለመስጠትና ዜጎች ሕክምናውን በአገር ውስጥ እንዲያገኙ ያስችላል የሚል ትልቅ ተስፋ እንዲጣልበት አድርጎታል ሲሉ አብራርተዋል።

ለሕክምናው የሚያስፈልጉ ቀሪ የሕክምና ግብአቶች ከውጭ መግባት የሚችሉበት መንገድ ከተመቻቸ ማዕከሉ በቀጣይ ዓመት ሕክምናውን የመስጠት አቅም ላይ ነው ብለዋል።



**ዶክተር ይስሀቅ ዩሱፍ**

የሕክምና መሣሪያዎችን አሟልቶ ሕክምናውን በሚቀጥለው ዓመት ለመስጠት ከመንግሥት የግዥ ኤጀንሲ ተቋምና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት ስምምነት በመደረሱ የግብዓት እጥረቱ በአጭር ጊዜ ሊፈታ እንደሚችልና ሕክምናው በቀጣይ ዓመት ሊጀምር እንደሚችል አመላክተዋል።ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ የውጭ አገራት የሕክምና ፕሮጀክቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለአካባቢው ማህበረሰብና ለአጎራባች አካባቢዎች የተለያዩ የጤና አገልግሎቶችን እየሰጠ እንደሚገኝ የገለጹት ኃላፊው፤ ዩኒቨርሲቲው የአዕምሮ ሕክምና ማዕከል እየገነባ እንደሆነም ተናግረዋል።

## በክልሉ ከ730...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ማስተማሪያ መጻሕፍት በሚቀጥሉት 10 ቀናት ሥርጭታቸው የሚከናወን ሲሆን፤ አንድ መጻሕፍ ለሁለት ተማሪዎች ይሰጣል ብለዋል፡፡

ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ያሉት መጻሕፍት በህትመት ወረፋ ምክንያት አሁን ላይ መድረስ አልቻሉም ያሉት ኃላፊው፤ በሚቀጥሉት ሦስት ወራት ህትመታቸው ተጠናቆ ለተማሪዎች መድረስ እንዲችሉ በትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡

ክልሉ በዕውቀትና ሥነምግባር የታነጸ ትውልድን ለመቅረጽ በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት የተማሪዎች መማሪያ መጻሕፍት ሲዘጋጅ ቆይቷል ብለዋል።

በክልሉ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ባለፈው ዓመት በሙከራ ደረጃ ተግባራዊ መደረጉን ያስታወሱት አቶ አብዱ፤ ውጤታማ መሆኑ በመረጋገጡ በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ወደ ሙሉ ትግበራ መሸጋገር መቻላቸውን አብራርተዋል።

ከአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት መጀመር ጋር ተያይዞ የተማሪዎች መማሪያ መጻሕፍት ህትመት ባለመጠናቀቁ ምክንያት የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዳይስተጓጎል ጊዜያዊ አማራጮችን በመጠቀም ትምህርቱ በየደረጃው እየተሰጠ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የክልሉ መንግሥት የመማሪያ መጻሕፍቱን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት ህትመት እያከናወነ እንደሚገኝ አብራርተው፤ የ139 ሺህ 770 መጻሕፍት ህትመት መጠናቀቅ የተወሰኑ የክፍል ደረጃዎችን ችግር ይቀርፋል ብለዋል፡፡

የክልሉ ትምህርት ቤቶች በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ውድመት የደረሰባቸው በመሆኑ መልሶ ለማቋቋም የሚሠሩ ሥራዎች ላይ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

## የቃሊቲ ቱሉ ዲምቱ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መንገዱ ባጋጠሙት ሁለት ዋና ዋና ችግሮች ምክንያት የግንባታ ሥራው ተጓትቶ እንደነበር የገለጹት አቶ እያሱ ከወሰን ማስከበር ጋር የተያያዘ እና የፋይናንስ ችግር መግጠሙን አብራርተዋል።

ከወሰን ማስከበር ጋር የተያያዘው ችግር የተፈጠረው በተለይ በመንገዱ የግራ ክፍል ከአቃቂ ቃሊቲ የሚመጣ ትልቅ የውሃ መስመር የነበረ በመሆኑ እሱ እስኪነሳ ድረስ ብዙ ጊዜ መውሰዱን ገልጸዋል። የወሰን ማስከበሩ ችግር ሙሉ በሙሉ ከተፈታ በኋላ ደግሞ የፋይናንስ ችግር ትልቅ እክል ሆኖ ነበር ብለዋል።

የፋይናንስ ችግሩ ያጋጠመው መንገዱ የሚገነባው ከቻይና ኤግዚም ባንክ በተገኘ ብድር የነበረ ሲሆን ባንኩ ለኮንትራክተሩ መክፈል የነበረበትን ክፍያ በወቅቱ ባለመክፈሉ ምክንያት ኮንትራክተሩ ሥራውን መቀጠል ባለመቻሉ ነው ብለዋል፡፡

ችግሩን ለመፍታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በስፋት ተነጋግረናል ያሉት አቶ እያሱ፤ መንገዱ ካለው ፋይዳና ኅብረተሰቡ ከሚያነሳው የልማት ጥያቄ አንጻር ምላሽ መሰጠት እንዳለበት በማመን የከተማ አስተዳደሩም ትኩረት ሰጥቶት ሲከታተለው ቆይቷል ብለዋል።

በዚህ መሠረትም ከቻይና ኤግዚም ባንክ ጋር ባለው የብድር ውል የፋይናንስ ክፍያው እስኪለቀቅ ድረስ ከመንግሥት በጀት በብድር ቀሪ ግንባታው እንዲከናወን በመፈቀዱ አሁን ላይ ግንባታው በፍጥነት እየተከናወነ ነው ብለዋል፡፡

የመንገዱ የግራ ክፍል የሙሌት ሥራዎች እየተገባደዱ ነው ያሉት አቶ እያሱ፤ አሁን ሁሉም ቦታዎች ላይ ሥራዎች ተከፋፍለው ምንም ዓይነት ችግር ሳይኖር በፍጥነት እና ባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ለትራፊክ ክፍት ለማድረግ እየተሠራ ነው የሚገኘው ብለዋል።

## የውጭ ግንኙነትን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ለማረጋገጥ እንደሚጠቀሙበት ገልጸዋል፡፡

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ ጉባኤው አዲስ አበባን የአፍሪካን የዲፕሎማሲ መዲናነትን የሚያጸና ነው፡፡ ከዋናው ጉባዔ ጎን ለጎን ከተለያዩ አገራት መሪዎች ጋር የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት ለማጠናከር ጠቃሚ የሆኑ ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎች ይሠራሉ፡፡ አገሪቱ ከሌሎች አገራት ጋር ያላትን የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር ይሠራል፡፡ የኢትዮጵያና የአፍሪካን የአረንጓዴ ልማት በማስፋፋት በዓለም አቀፍ ደረጃ ላሉ አካባቢያዊ ችግሮች መፍትሄ በሚሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚመክርና ኢትዮጵያም ልምድ የምታጋራ ትሆናለች፡፡ አፍሪካውያን ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ እንዲኖር ላደረጉት ድጋፍም ምስጋና ይቀርባል፡፡

አምባሳደር መለስ በመግለጫቸው እንደተናገሩት፤ 42ኛው የአፍሪካ ኅብረት የሥራ አስፈጻሚ ምክር ቤት ከዛሬ የካቲት ስምንት ጀምሮ ለተከታታይ ሁለት ቀናት መካሄድ ይጀምራል፡፡ በመሪዎች ደረጃ ደግሞ ከየካቲት አስር ጀምሮ ለሁለት ቀናት ይካሄዳል፡፡ ጉባኤውን በበቂ ሁኔታ ለማጠናቀቅ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል፡፡ እንደ ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያሉ ተቋማት ሰፊ ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎችን እንዲሠሩ ዕድል ይፈጥራል፡፡

በባለሙያዎች ደረጃ በሚካሄዱ ስብሰባዎች ኢትዮጵያ ንቁ ተሳትፎ እያደረገች ትገኛለች ያሉት አምባሳደሩ፤ በተለየ መልኩ ዝግጅት እያደረገች ነውም ብለዋል፡፡

በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን የሚመራ የኢትዮጵያ ልዑክ ከዛሬ ጀምሮ መሳተፍ እንደሚጀምር ገልጸውም፤ ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ጉባዔውን በመጠቀም በሁለትዮሽና በባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ዙሪያ ጠንካራ ውይይት ያደርጋሉ ብለዋል፡፡

ስብሰባው ያለፈውን ዓመት ዕቅድ ይቃኛል፤ በመጪው ጊዜ ትልምና ዕቅድ ላይም ውይይት የሚያደርግ ነው፡፡ 35 ርዕሳነ ብሔሮች፣ የ11 አገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች፣ አራት ጠቅላይ ሚኒስትሮች፣ 13 ቀዳማዊ እመቤቶች፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ጨምሮ የአሥር ዓለም አቀፍ ድርጅት የሥራ ኃላፊዎች እና ስድስት የአፍሪካ ኅብረት አባል ያልሆኑ አገራት በጉባዔው ይሳተፋሉ ብለዋል።

# ሁሉም ተቋማት የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት የግዥ ሥርዓትን እንዲጠቀሙ ባለሥልጣኑ አሳሰበ

**- ሥርዓቱ እስከ 25 በመቶ የሚሆነውን የመንግሥት በጀት መቆጠብ ያስችላል**

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ሁሉም የመንግሥት ተቋማት የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት የግዥ ሥርዓትን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን አሳሰበ።የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት የግዥ ሥርዓት ከአምስት እስከ 25 በመቶ የሚሆነውን የመንግሥት በጀት መቆጠብ እንደሚያስችልም ጠቁሟል፡፡

የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀጂ ኢብሳ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ የመንግሥት የግዥ ሥርዓትን ከሌብነት የጸዳና ውጤታማ ለማድረግ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከባለፉት ዓመታት ጀምሮ በትኩረት እየሠራ ነው።በተለይ ባለስልጣኑ ተግባራዊ እያደረገ ያለው የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት የግዥ ሥርዓት ከአምስት እስከ 25 በመቶ የሚሆነውን የመንግሥት በጀት መቆጠብ ያስችላል።

እንደ አቶ ሀጂ ገለጻ፤ ከአገሪቱ በጀት 70 በመቶ የሚሆነው ለግዥ የሚውል ነው።በጀቱን በአግባቡ ለታለመለት አላማ ለማዋል በተለይ የመንግሥት የኤሌክትሮኒክስ የገዥ ሥርዓት ወሳኝ ነው።ይህ ሥርዓት ዓለም የግልጸኝነት አሠራር የዘረጋበትና ብልሹ አሠራርን ያስቀረበት ነው።ኢትዮጵያም ይህንኑ አሠራር እየተገበረች ነው።

ኢትዮጵያ የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት የግዥ ሥርዓትን በመተግበር ከአፍሪካ ስድስተኛ አገር ናት ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከሦስት ዓመት በፊት በዘጠኝ መስሪያ ቤቶች ላይ በሙከራ ደረጃ የተጀመረው የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት በአሁኑ ጊዜ ከ74 የፌዴራል ተቋማት 69 የሚሆኑት የተሳካ ግዥ እየፈጸሙ ነው ብለዋል።

ከእነዚህም ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ከተለመደውና አድካሚ ከሆነው የማንዋል (የወረቀት) ግዥ ሥርዓት በመውጣት የተሳካ ግዥ እየፈጸሙ መሆኑን ጠቅሰዋል። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የአደጉ አገሮች በደረሱበት ልክ ግዥ እየፈጸመ ነው ሲሉ ጠቅሰዋል።

በመንግሥት የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት ውስጥ ለመግባት ሚኒስቴር መስሪያቤቶች ጭምር እያስቸገሩ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ሀጂ፤ ስማቸውን ለመግለጽ ያልፈለጓቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች የባለስልጣኑ ባለሙያዎች ወደ ተቋማቱ ሲሄዱ እስከማባረር የደረሱ መኖራቸውን ገልጸዋል።

ከ160 የፌዴራል ተቋማት 19 መስሪያ ቤቶች የግዥ ዕቅድ የላቸውም።አንድ ተቀጣሪ የመንግሥት ሠራተኛ ደመወዙን በእቅድ በሚመራበት በዚህ ወቅት ትልቅ የአገር ሀብት የሚያንቀሳቅስ የፌዴራል ተቋም ያለ እቅድ ግዥ መፈጸም ትልቅ ክፍተት መሆኑን አስረድተዋል።እነዚህን ተቋማት ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር የማስተካከያ እርምጃ ይወሰድባቸዋል ነው ያሉት፡፡

ወደ ኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓቱ ለመግባት የስድስት አገራት ተሞክሮ እንደተወሰደ ያስታወሱት አቶ ሀጂ፤ ሥርዓቱ እንደ አገር ከተመደበው በጀት አምስት በመቶ እስከ 25 በመቶ የሚሆነውን በጀት መቆጠብ የሚያስችል ነው። ለምሳሌ የኢትዮጵያ የአንድ ዓመት በጀት 560 ቢሊዮን ብር ቢሆን 25 ከመቶ ተቆጠበ ማለት 140 ቢሊዮን ብር እንደማለት መሆኑን አብራርተዋል። ይህም የአማራ፣ የኦሮሚያና የደቡብ ክልል የዓመት በጀታቸው እንደማለት ነው ብለዋል፡፡

አቶ ሀጂ፤ እንደ ኮሪያ ያሉ አገሮች 25 በመቶ በጀታቸው በኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት ይቆጥባሉ።ሰሜን ኮሪያ ከወረቀት ብቻ እስከ ስምንት መቶ ሚሊዮን ዶላር ብር በዓመት ትቆጥባለች።በኢትዮጵያም ይህን በመተግበር የወረቀትን ብክነት፣ ከተለያዩ ቦታዎች ለጨረታ የሚወጣው የትራንስፖርትና መሰል ወጪን ማዳን የሚያስችል ነው፡፡

አሰልቺ የሆነውን የወረቀት ጨረታ በማድረግ ሁለት ሦስቱን በማሳለፍ የጥቅም ትስስር የሚፈጠርበትን የግዥ ሂደት ማቆም አስፈላጊ ነው ያሉት አቶ ሀጂ፤ የግብይት ሥርዓቱ አሳታፊ የሆነና ከሙስና የጸዳ ማድረግ ያስፈልጋል።ሥርዓቱን የማይቀበሉት አካላት ጥቅማችን ይቀራል ከሚል እሳቤ መሆኑን ገልጸዋል።

የኤሌክትሮኒክስ የግዥ ሥርዓት ላለፉት ሁለት መቶ ዓመት አካባቢ ድረስ ኢትዮጵያ ከለመደችበት የማንዋል ወይም የወረቀት የግዥ ሥርዓትና ከብልሹ አሠራር የምትላቀቅበት በመሆኑ ሁሉም ሊቀበለውና ሊተገብረው ይገባል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኅብረቱ ጉባኤ የተሳካ እንዲሆን!

የአፍሪካ ህብረት የአህጉሪቱ ጉዳይ የሚመከርበት ጉባኤ በየአመቱ በፈረንጆቹ አዲስ አመት የመጀመሪያ ወራት በአዲስ አበባ ይካሄዳል::በዚህ ጉባኤ የአፍሪካ የሰላምና ፀጥታ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳይ አጀንዳ በማድረግ መሪዎቹ ይወያያሉ::ውሳኔም ያሳልፋሉ::የኅብረቱ አባል ሃገራትም እንደየሃገራቸው ተጨባጭ ሁኔታ ውሳኔዎቹን ለመተግበር ጥረት ያደርጋሉ፡፡

ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አንድነት ኋላም ለአፍሪካ ኅብረት ምስረታ ከፍተኛውን ሚና መጫወቷ በታሪክ ይታወቃል::አዲስ አበባም የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ናት::ሃገራችን ከ50 ዓመታት በላይ እድሜ ላስቆጠረው አህጉራዊ ተቋም እና ለአፍሪካዊያን በተለያየ ስርዓተ መንግስት የማይለዋወጥ ድጋፍ አድርጋለች፤ አሁንም እያደረገች ትገኛለች፡፡ወደፊትም ታደርጋለች፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብም በተለይ ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ ላለፉት በርካታ አስርት ዓመታት የኅብረቱ መሪዎች ጉባኤ በአዲስ አበባ ሲካሄድ በኢትዮጵያዊ ስነምግባርና መስተንግዶ ባረፉባቸው ሆቴሎች ፣ በሚዘዋወሩባቸው የገበያ መደብሮችና መንገዶች በአክብሮት አስተናግዷቸዋል፡፡አሁንም ያስተናግዳቸዋል፡፡

ከመጪው የካቲት 10 እስከ 12 ቀን 2015 ዓ.ም 36ኛው የአፍሪካ መሪዎች ጉባኤ ይካሄዳል::ከመሪዎቹ ጉባኤ ቀደም ብሎ ደግሞ የካቲት 8 እና 9 ቀን 2015 ዓ.ም 42ኛ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ ይካሄዳል::እነዚህ ጉባኤዎች የተሳኩ እንዲሆኑ መንግስት እንዲሁም የፀጥታ ተቋማት እና ሆቴሎች በቂ ዝግጅት አድርገው እየተጠባበቁ ነው፡፡

የከተማዋን ፀጥታ አስተማማኝ ለማድረግ እና ለእንግዶች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እንዲቻል የፀጥታ መዋቅሩ በቂ ዝግጅት አድርጓል::የፀጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ ሃይል በአዲስ አበባ ዋና ዋና መንገዶች ላይ ያደረገውን የአጀብና የፀጥታ ሥራዎች የተግባር ልምምድ በስኬት ማጠናቀቁን አስታውቋል፡፡

የፀጥታና ደህንነት የጋራ ግብረ ሃይሉ ታላላቅ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ጉባዔዎችን በሰላም እንዲጠናቀቁ ሥራውን የሚመጥን ተግባራዊ ልምምድ አድርጓል::መጪውን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባኤን ምክንያት በማድረግም የአጀብ እና የፀጥታ ስራዎችን መሰረት ያደረገ ልምምድ ያደረገው የእንግዶች ደህንነት እንዲጠበቅና አስተማማኝ የፀጥታ ሁኔታ በከተማዋ እንዲኖር ለማስቻል ነው::የከተማዋ ነዋሪዎችም ከዚህ በፊት በኅብረቱ ጉባኤ ያደርጉት እንደነበረው ከፀጥታ አካላት ጋር በመናበብ የተለመደውን ትብብራቸውን አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ይጠበቃል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ በመዲናይቱ የሚደረጉ አህጉራዊና አለምአቀፋዊ ጉባኤዎችና ሁነቶች በተሳካ ሁኔታ እንዲፈፀሙ ሁሌም ተባባሪ ነው::የራሱ ተቋም የሆነው የአፍሪካ ኅብረት የሚያካሂዳቸው ጉባኤዎች ደግሞ ይበልጥ በእኔነት ስሜት ከፀጥታ ኃይሎች ጋር በመተባበር በሰላም እንዲጠናቀቁ መስራት ይጠበቅበታል፡፡

በመዲናይቱ የሚካሄዱ ጉባኤዎች ለከተማዋ ገቢ ያስገኛሉ::ወደ ስብሰባ የሚመጡ ሰዎች በሚያርፉባቸው ሆቴሎች አካባቢ ብቻ ሳይሆን ታላላቅ የገበያ መደብሮች ግብይት ያካሂዳሉ::በዚህ ወቅት ሕዝቡ በተለይ ደግሞ አሽከርካሪዎች ለእንግዶች ቅድሚያ በመስጠት ኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነት በተግባር ማሳየት ይገባቸዋል፡፡

በከተማዋ ማንኛውም ዓይነት የፀጥታ ችግር ካጋጠመ የሃገር ገፅታ ነው የሚበላሸው፤ ኢትዮጵያዊያን ለዘመናት የገነቡት የእንግዳ ተቀባይነት እሴት ነው አደጋ ላይ የሚወድቀው፡፡ስለዚህ ይህ እንዳይሆን ከተራ የስርቆት ወንጀል ጀምሮ አንድም የፀጥታ ችግር እንዳያጋጥም ሕዝቡ ከፀጥታ አካላት ጋር ተባባሪ ሆኖ መስራት አለበት፡፡

በከተማዋ ያሉ አሽከርካሪዎች ሆነ ተጠቃሚዎች ከፀጥታ አካላት የሚሰጣቸውን መመሪያና ተለዋጭ መንገድ በመጠቀም የትራፊክ ፍሰቱን ለእንግዶች የተመቸ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::ታጋሽና አስተዋይ ሆነው ለሃገራቸው የመልካም ስም አምባሳደር ሊሆኑ ይገባል፡፡

እንግዶች በሚያርፉባቸው ሆቴሎችና መዝናኛ ቦታዎች፤ የገበያ ቦታዎች፣ ፓርኮችና ሙዚየሞች ለእንግዶች ምቾት መስራት አለባቸው::በእነዚህ ቦታዎች እንግዶቹ የሚፈልጓቸውን ከማቅረብ ጀምሮ በቋንቋ አለመግባባት ክፍተት እንዳይኖር የአፍሪካ ሃገራት በሚጠቀሙባቸው ቋንቋዎች በማስተናገድ ጥሩ መግባባት በመፍጠር ገቢም መልካም ገፅታም መገንባት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ 36ኛው የኅብረቱ የመሪዎች ጉባኤ በተሳካ ሁኔታ ያለምንም የፀጥታ ችግር እንዲጠናቀቅ መላው የከተማዋ ህዝብ ከፀጥታ ደህንነት የጋራ ግብረ ኃይል እና ከፀጥታ ሰራተኞች የሚሰጡትን መመሪያዎችና ትእዛዞች መተግበር አለበት::ይህን መመሪያና ትእዛዝ መፈፀም ለከተማዋ ሕዝብ አዲስ አይደለም::ላለፉት በርካታ አስርት ዓመታት ያደርገው የነበረ እና አፍሪካዊያንም የሚያውቁት ስለሆነ ይህንን አጠናክሮ በዚህ ጉባኤም ማሳየት ይቻላል፤ይገባልም!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የጠቅላይ ሚኒስትሩ የአውሮፓ ሀገራት ጉብኝት እና ፋይዳው

**መሳኩ ኤሮሴ**

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ሲካሄድ የቆየው የእርስ በርስ ጦርነት አሉታዊ ተጽዕኖ ካሳረፈባቸው ዘርፎች መካከል ዲፕሎማሲ አንዱ ነው:: ጦርነቱ ሀገሪቱ ከሌሎች ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት እንዲሻከር አድርጓል:: በተለይም ኢትዮጵያ ከምዕራቡ ዓለም ሀገራት ጋር የነበራት ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረውና የጋራ ጥቅምን መሰረት ያደረገ ግንኙነት እንዲሻከር ምክንያት ሆኖ ቆይቷል:: ግንኙነት ከመሻከሩ ባሻገር ምዕራባዊያኑ ከፍተኛ ጫና ሲያሳድሩባት እንደቆዩ የአደባባይ ሚስጢር ነው::

በፌዴራል መንግስት እና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት ኢትዮጵያ ከገባችበት የዲፕሎማሲ ቀውስ በመውጣት ከተለያዩ ሀገራት ጋር ያላት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ዳግም እንዲሻሻል እድል ፈጥሯል:: በተለይም ጦርነቱ በሰላም ድርድር እንዲቋጭ እና ያልተገደበ ሰብዓዊ እርዳታ እንዲቀርብ በመንግስት ላይ ጫና ሲያደርጉ ከነበሩ ከምዕራቡ ዓለም ሀገራት ጋር ያለው የዲፕሎማሲ ግንኙነት መሻሻል ማሳየት ጀምሯል::

ከሰላም ስምምነቱ በኋላ በተለይም የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በአሜሪካና አውሮፓ ሀገራት ያደረጉት ጉብኝቶች የሀገሪቱ የተቀዛቀዘው ዲፕሎማሲ እንዲነቃቃ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል:: በስምምነቱ ማግስት የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ከአፍሪካ ሀገራት መሪዎች ጋር ባደረጉት ጉባኤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ተገኝተው የሰሯቸው የዲፕሎማሲ ስራዎች በሁለቱ ሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ላይ አጥልቶ የነበረውን ጥላ የገፈፈ ከመሆኑም ባሻገር የአሜሪካንን ፈለግ ከሚከተሉ የአውሮፓ ሀገራት ጋርም የዲፕሎማሲ ግንኙነት እንዲያንሰራራ በር የከፈተ ነበር ማለት ይቻላል::

> ሀገራቱ ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን የሁለትዮሽ ትብብር ለማሳደግ በከፍተኛ ዲፕሎማቶች አማካኝነት የገቡት ቃል ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲ ረገድ ያደረገቻቸው እልህ አስጨራሽ ጥረት ፍሬ የምትቋደስበት ደረጃ ላይ እንዳለች ያሳያል

ባለፈው ሳምንት ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጣሊያን፣ ማልታና ፈረንሳይ ያደረጉት ይፋዊ ስራ ጉብኝት ኢትዮጵያ ከሀገራቱ ጋር በንግድ፣ በኢንቨስትመንት፣ በቱሪዝም፣ በሎጂስቲክስ እና በጸጥታ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ትብብር ማሳደግን ጨምሮ በሌሎች የሁለትዮሽ ጉዳዮች ላይ ተወያይተዋል:: በዚህ ጉብኝት ለኢትዮጵያ ከፍ ያለ ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ የተገኘበት ከመሆኑም ከሀገራቱ ጋር የቆየው ዘመን ተሻጋሪ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የበለጠ እንዲያንሰራራ ከፍተኛ ሚና የተጫወተ ነው::

በጣሊያን ባደረጉት ጉብኝት የ180 ሚሊዮን ዩሮ የረጅም ጊዜ ቀላል ብድርና ቀጥተኛ ድጋፍ የተገኘበት ሲሆን፤ የጣሊያን መንግስት በቀጣይም ለኢትዮጵያ ሌሎች ድጋፎችን ለማድረግ ማረጋገጫ የሰጠበት መሆኑ ተነግሯል:: ድጋፉ ጉዳት የደረሰበትን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መልሶ ለመገንባት እና የኢኮኖሚ ሪፎርሙን አጠናክራ እንድትቀጥል አቅም የሚፈጥር ይሆናል::

በፈረንሳይ ያደረጉት ጉብኝት የሁለቱን ሀገራት ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ለማጠናከር ያለመ ስለመሆኑ እና በዚህ ረገድም ውጤት የተገኘበት ስለመሆኑ የብሄራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምህረቱ ለሚዲያዎች ተናግረዋል:: መንግስት ተግባራዊ እያደረገ ካለው የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራም አንዱ ዋነኛው ሃሳብ ኢትዮጵያ ያለባትን እዳ የማሸጋሸግ ሲሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ እዳ ሽግሽግን የጋራ ማዕቀፍን የሚመሩት ፈረንሳዮች ናቸው:: ስለዚህ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ ያለባትን እዳ ለማሸጋሸግ ፈረንሳይን የማግባባት ስራ መስራታቸውንና በዚህም ውጤት መገኘቱ ተጠቁሟል::

በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ዘርፎች ተሰማርተው ካሉ የፈረንሳይ ኩባንያዎች ኃላፊዎች ጋር ውይይት መደረጉ የተጠቆመ ሲሆን፤ በሎጂስቲክስ፣ በሚዲያ፣ በኢነርጂ፣ በሀይል አቅርቦት ዘርፍ እንዲሁም በባቡር ዘርፍ የፈረንሳይ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ለማድረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ የጀመሩ ሲሆን፤ እነዚህን እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ በመሪዎች ደረጃ ውይይት ስለመደረጉ ተገልጧል:: በፈረንሳይ መንግስት ሚኒስትሮችና በኢትዮጵያ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች መካከል ሰፊ ውይይት ስለመደረጉ ተነግሯል::

ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ ከምዕራቡ ዓለም ሀገራት የሚገኘው የልማት እና ሰብዓዊ እርዳታ ረገድ መሻሻል ከመታየቱም ባሻገር፤ በምዕራቡ ዓለም ከሚዘወሩት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና አጋሮች የሚገኘው የሰብአዊ እና የልማት ዕርዳታ በኩል አዎንታዊ ውጤቶች እየታዩ ነው።

የሰላም ስምምነቱ በተፈረመ ማግስት በሰብዓዊ እና የልማት እርዳታ ላይ አዎንታዊ ውጤቶች ከመመዝገባቸው ባሻገር፤ የተለያዩ ሀገራት ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናትም በኢትዮጵያ ጉብኝት ማድረጋቸው የሰላም ስምምነቱ ያስገኘው ሌላኛው ትሩፋት ነው:: በሰላም ስምምነቱ ማግስት የቻይና፣ የጀርመን እና የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ጉብኝት ማድረጋቸው ሀገራቱ ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር ፍላጎት እንዳላቸው የሚያሳይ አንዱ ምልክት ተደርጎ የሚወሰድ ነው::

ሀገራቱ ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን የሁለትዮሽ ትብብር ለማሳደግ በከፍተኛ ዲፕሎማቶች አማካኝነት የገቡት ቃል ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲ ረገድ ያደረገቻቸው እልህ አስጨራሽ ጥረት ፍሬ የምትቋደስበት ደረጃ ላይ እንዳለች ያሳያል። በተለይም አዲሱ የቻይና ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቺን ጋንግ በቅርቡ በኢትዮጵያ ያደረጉት ጉብኝት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የዲፕሎማሲ ክንውን ነው:: ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያን አስቀድመው መጎብኘታቸው በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የማይናወጥና ጠንካራ ግንኙነት ያሳያል ሲሉ የጉብኝቱን ፋይዳ አብራርተዋል::

ኢትዮጵያ በሀያላን አገሮች መካከል ያለው ፉክክር ሰለባ እንዳትሆን የምትታወቅበትን የገለልተኝነት አቋሟን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ምሶሶ አድርጋ በመያዝ ከምዕራቡም ሆነ ከምስራቁ ንፍቀ ክበብ ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ማጠናከር ይገባል:: ከሁሉም ሀያላን ሀገራት ጋር በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ሚዛናዊ እና ፍትሃዊ አጋርነትን ለማስቀጠል የጀመረችውን ጥረት አጠናክራ መቀጠል አለባት:: የገለልተኝነት አቋሟ ከሀያላን ሀገራት አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳይደርስባት ከማገዙም ባሻገር ኢትዮጵያ በሀያላን ሀገራት መካከል ያለውን ፉክክር ወደ መልካም እድል መቀየር እንድትችል እድል ይፈጥርላታል::

# ተጠየቅ

# «ከአሜሪካ እና ቻይና በመቀጠል የሚትዎሮሎጂ መሰረተ-ልማትን የያዘ ህንፃ እየተገነባ ነው»

*- አቶ ፈጠነ ተሾመ*
*የኢትዮጵያ ሚትዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር*

ክፍለዮሐንስ አንበርብር



በመላ ሀገሪቱ ያለውን የአየር ሁኔታ ለመከታተል የሚረዱ 12 ዘመናዊ ራዳሮች የሚያስፈልጉ መሆኑ በጥናት ተለይቷል:: በሚቀጥሉት 10 ዓመታት የሚከናወኑ፣ የሚትዎሮሎጂ ምልከታና ትንቢያን የሚሰጡ ራዳሮች በመተከል ላይ ናቸው

የኢትዮጵያ የሚትዎሮሎጂ ዕይታዎች በፈረንጆቹ አቆጣጠር፣ በ19ኛው ክፍለ ዘመን በአውሮፓ ሚሲዮናዊያን እንደተጀመረ ይነገራል:: ይህን እንደመነሻ አርሾ በመጠቀም ሌሎች አማራጮችን መመልከት ተጀመረ:: የተወሰኑ ማዕከላትም እስከ 1890ዎቹ ድረስ መረጃ ነበራቸው:: በ1951 ግን የሚትዎሮሎጂ አገልግሎት በሲቪል አቬዬሽን ባለስልጣን ውስጥ ለሙከራ ተጀመረ:: በሂደትም ብዙ መረጃዎችን እና ልምዶችን ማግኘት ተቻለ::

እውቀት እና ግንዛቤው እያደገ በመምጣቱ በ1971 በተጀመረበት ሲቪል አቬዬሽን ሥር እንዲተዳደር ሆኖ ተቋቋመ:: በ1980 ብሔራዊ ሚትዎሮሎጂ ኤጀንሲ በሚል ሥያሜ ራሱን ችሎ በአዋጅ 201 መሰረት ተቋም ሆነ:: ከዚህን ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያን ያማከለ መረጃ በስፋት ማሰራጨት ጀመረ:: በ2021 ደግሞ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት በሚል በአዋጅ 1263/2021 ተቋቋመ::

ዘመናትን በመሻገር ዕለታዊውን የአየር ሁኔታ ከመተንበይ አንሥቶ እስከ ረጅም ጊዜ የአየር ጠባይ ትንበያ ድረስ በመተንተንና በመገምገም፤ የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ሊያሳድሩ የሚችሉትን ተጽዕኖዎች በመከታተልና አስቀድሞ በመተንበይ የደንበኞችንና የባለ ድርሻ አካላትን ፍላጎት ለማርካት በትጋት በመሥራት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው - የኢትዮጵያ ሚትዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት።

ኢትዮጵያ በዓመት ውስጥ በተጽዕኗቸው የተለዩትን ሦስት ወቅቶች በሚያስተናግድ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥና የአየር ጠባይ ውስጥ መሆኗ ይታወቃል:: እነዚህ ወቅቶች በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ባላቸው አንድምታ የተለዩ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የተለያዩ ተጽዕኖዎች ያሏቸው በመሆኑ የኢትዮጵያ ሚትዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ሳይንሳዊ ዘዴዎችን በመከተልና የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችና ግብዓቶችን በመጠቀም በተለያዩ የጊዜ ቀመር የተለዩ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያዎችን በማዘጋጀት፤ ከተጠቃሚዎች ጋር በመመካከር የመገናኛ ብዙኃን እና ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም ለተጠቃሚዎች የሚያሰራጭ መሆኑም ይታወቃል::

በዛሬው ዕትማችን የኢትዮጵያ ሚትዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለዓመታት ያለፈባቸውን ተግባራትና እያስገኛቸው የሚገኙ ውጤቶችን፤ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ያለውን ተናብቦ የመስራት ሂደት፤ በቴክኖሎጂ የደረሰበትን ደረጃ እና በቀጣይ ሊያሳካቸው የሚያስባቸውን እቅዶች አንስተን ከዋና ዳይሬክተሩ አቶ ፈጠነ ተሾመ ጋር ቆይታ አድርገናል::

**አዲስ ዘመን፡- በጋውን አስመልክቶ የሰጣችሁት ትንቢያ እና ያለፉት ስድስት ወራት ሂደቶች ምን ያክል ተጣጥመዋል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ኢንስቲትዩታችን በዘንድሮው የበጋ ወቅት ትንበያው ሊፈጠር የሚችለውን የዓየር ሁኔታ በጊዜና በቦታ ያለውን ስርጭትና ተጽዕኖን በተመለከተ በመስከረም 2015 ዓ.ም የወቅት ትንበያ ሰጥቶ ነበር። በተጨማሪም በየጊዜው የወቅት አጋማሽ፣ ወርኃዊና የአሥር ቀናትን፣ የሦስት ቀናትንና ዕለታዊ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያ መስጠቱ ይታወቃል:: አሁን ወደ ኋላ ተመልሰን ኢንስቲትዩቱ የሰጠውን የበጋ ትንበያና በተጨባጭ የነበረውን የአየር ሁኔታ ስንገመግም ከሞላ ጎደል የተጣጣሙ ሆነው አግኝተናቸዋል። ይህም ለተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች በተለይም ለግብርናው ዘርፍ የበኩላችንን አስተዋጽዖ እንድናደርግ፤ ተጠቃሚዎችና ባለ ድርሻ አካላትም መረጃዎቻችንን በይበልጥ እንዲጠቀሙ አስችሏል:: በቀጣይም የምንሰጣቸው ትንቢያዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናል::

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ የበልግ ወቅት የአየር ትንቢያ ምን ያመለክታል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** የበልግ 2015 ዓ.ም ትንበያ እንደሚያሳየው መጪው በልግ አሁን በትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት እና የህንድ ውቅያኖስ መደበኛ የባህር ወለል ሙቀት መጠን መደበኛ ሆኖ እንደሚቆይ የሚያመለክት በመሆኑ የወቅቱ ዝናብ አጀማመር ሊዘገይ እንደሚችልና በአወጣጥ ረገድ ግን ጊዜውን የጠበቀ እንደሚሆን ይጠበቃል::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ኢንስቲትዩታችን ከሚሰጠው አጠቃላይ የበልግ ትንበያ በተጨማሪ በመጪው በልግ በሀገራችን የተለያዩ ቦታዎች ሊፈጠሩ የሚችሉትን የአየር ሁኔታ ገጽታዎችን አስቀድሞ በመተንበይ የቅድመ - ማስጠንቀቂያ እና የትንበያ መግለጫዎች ይሰጣል:: በመሆኑም ሕብረተሰቡ ይህንኑ መረጃ እንዲጠቀምና የሚሰጡትን የቅድመ-ማስጠንቀቂያ መግለጫዎችን በቅርበት መከታተል አለበት::

**አዲስ ዘመን፡- ብዙ ጊዜ የምትሰጡት ትንቢያ እና እውነታው የተራራቀ ነው የሚል ትችት ይቀርባል:: በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ትንቢያዎች በአንድ ጊዜ ብቻ ተሰጥተው የሚጠናቀቁ አይደሉም:: በየጊዜው መረጃዎች የሚታዩና የሚተነተኑ ናቸው:: የአየር ጸባይ በባህሪው የሚቀያየርና ትንተናዎችን የሚፈልግ ነው:: ይህ በአንድ ጊዜ ስራ ብቻ ተሰርቶ የሚቀመጥና በአንድ ጊዜ በቂ አይደለም::

ስለዚህ የአየር ትንበያ መረጃዎች ከእውነታው ጋር የተራራቁ ናቸው የሚለው አግባብ አይደለም:: የምንሰጣቸው ትንበያዎች የሚጠበቀውን ውጤት እየሰጡ ነው:: ለአብነት እኛ በዘንድሮው የበጋ ወቅት ትንበያው ሊፈጠር የሚችለውን የዓየር ሁኔታ፣ በጊዜና በቦታ ያለውን ስርጭትና ተጽዕኖን በተመለከተ በመስከረም ወር (2015 ዓ.ም) የወቅት ትንበያ ሰጥተን ነበር። አሁን ላይ ሁኔታውን ስንገመግመው ያገኘነው ውጤት ትንቢያችንና መሬት ላይ ያለው እውነታ የተጣጣሙ ናቸው:: ቀደም ሲል ስንሰጣቸው የነበሩት መረጃዎችም በተመሳሳይ የተጣጣሙ ነበሩ:: በየጊዜው አዳዲስ ቴክሎጂዎችን እየተጠቀምን በመሆኑ የመረጃው ጥራት በዚያው ልክ እያደገ መጥቷል::

**አዲስ ዘመን፡- በምትሰጡት የአየር ሁኔታ ትንበያ የትኞቹ ዘርፎች የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናሉ?**

**አቶ ፈጠነ፡-** እኛ በምንሰጠው መረጃ የተለያዩ፣ በርካታ ዘርፎች ተጠቃሚ ናቸው:: በግብርናው ዘርፍ ብንሄድ ከሚኒስቴሩ ጀምሮ በየደረጃው ያሉ አካላት እየሰሩ ያሉት በትንቢያው መሠረት ነው:: ከአውሮፕላን በረራ ጋር በተያያዘ ሰፋፊ መረጃዎችን እንሰጣለን:: ይህም በጣም በስኬታማ መንገድ የሚነሳ ነው:: በጤና ዘርፍም የሚሰጠው ፋይዳ እጅግ ሰፊ ነው:: ከውሃ ሃብት መንከባከብም ሆነ መጠቀም ጋርም በእጅጉ የሚጠቅም መረጃ የሚገኘው ከዚሁ ትንበያ በመነሳት ነው:: ጎርፍ እና መሰል አደጋዎችን በመከላከል ረገድም የምንሰጣቸው ትንበያዎች ፋይዳቸው የጎላ ነው::

በአየር ጸባይ ትንበያ የማይጠቀም አካል የለም:: ለዚህም በየጊዜው መረጃዎችን ተደራሽ እያደረግን ነው:: ይህ ትንቢያ አንዱን ለብቻ ነጥሎ የበለጠ ተጠቃሚ የሚያደርግ አይደለም:: አንዱ ከሌላው ጋር የተሳሰረ በመሆኑ ሁሉም ተጠቃሚ ነው:: እኛም የምንሰጠው መረጃ ሁሉም ተቋማትና አካባቢዎች እንደየነባራዊ ሁኔታዎች እንዲጠቀሙበት ነው::

**አዲስ ዘመን፡- የአየር ትንበያን ከመተንተንና ከማወቅ አኳያ ዘመናዊ ራዳሮች ያስፈልጋሉ:: በዚህ ረገድ ምን ተሠርቷል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** በመላ ሀገሪቱ ያለውን የአየር ሁኔታ ለመከታተል የሚረዱ 12 ዘመናዊ ራዳሮች የሚያስፈልጉ መሆኑ በጥናት ተለይቷል:: በሚቀጥሉት 10 ዓመታት የሚከናወኑ፣ የሚትዎሮሎጂ ምልከታና ትንቢያን የሚሰጡ ራዳሮች በመተከል ላይ ናቸው:: እነዚህ ትንበያዎችን ከማጠናከር አንፃር ለግብርና፣ ውሃ፣ ጤና እና ሌሎች ዘርፎችንም ታሳቢ ያደረጉ ሥራዎች እየተከወኑ ናቸው:: በእነዚህ ዓመታት ውስጥም የአየር ሁኔታን ለመከታተል የሚረዱ ራዳሮችን ከአንድ ወደ ስምንት ለማሳደግ መንግስት በትኩረት እየተንቀሳቀሰ ሲሆን፤ ከተለያዩ ለጋሽ ሀገራት ጋርም ስምምነት ተደርጎ ሦስት የአየር ሁኔታ መከታተያ ራዳር ለመትከል በሂደት ላይ ነን::

ቀደም ሲል በባህር ዳር፣ ሻውራ ከተተከለው ራዳር በተጨማሪ የማዕከላዊ ኢትዮጵያን የአየር ሁኔታ ለመከታተል በአማራ ክልል፣ ሰሜን ሸዋ ዞን፣ እነዋሪ፤ በደቡብ ኢትዮጵያ ደግሞ አላባ ቁልቶ፤ እንዲሁም በምዕራብ ኢትዮጵያ ኢሉ አባቦራ፣ በኮ የሚባል ተራራ ላይ ተከላ የማከናወን ተግባራት በጥሩ ሁኔታ እየተከናወኑ ናቸው:: እነዚህ ራዳሮች እስከ 250 ኪሎ ሜትር ድረስ መረጃ ይሰበስባሉ:: እነዚህ መረጃዎች ከተሰበሰቡና ከተተነተኑ በኋላ የሚኖራቸው ትልቅ ፋይዳ ከፍተኛ ሲሆን፤ ራዳሮቹ ሲተከሉ የኢትዮጵያን መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ መሠረት ባደረገ መልኩ መሆኑንም ማወቅ ያስፈልጋል::

**አዲስ ዘመን፡- ራዳሮቹ መረጃ ለመሰብሰብ ብቻ የሚፈይዱ ናቸው?**

**አቶ ፈጠነ፡-** እነዚህ ራዳሮች ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባታቸው በፊት "ምን ጥቅም ይሰጣሉ?" የሚለውን

# ተጠየቅ



በባለሙያዎች አስጠንተናል:: ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ራዳሮች ደመና ለማበልፀግ በሚደረገው ጥረት ትልቅ ፋይዳ ይኖራቸዋል:: አስር የደመና ዓይነቶች አሉ:: እነዚህ ራዳሮች ደግሞ በተለይም ዝናብ ሰጪ የሆነውን ቁልል ደመና በመለየት ትልቅ አገልግሎት የሚሰጡ ይሆናል:: ይህም ኢትዮጵያን ደመናን በማበልጸግ እና አስፈላጊውን የኬሚካል ርጭት ለማድረግ ዝናብ ለማዝነብ ያስችላታል::

ደመናን ለማበልፀግ የተሞከረው ባህር ዳር ሻውራ ላይ ብቻ በነበረው ራዳር ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ግን በእነዋሪ፣ ምዕራብ ወለጋ እና ደቡብ ኢትዮጵያ የሚተከሉት ራዳሮች ለዝናብ ማበልጸግ እና አየር ሁኔታን ለመተንተንና ለመከታተል ትልቅ ፋይዳ ይኖራቸዋል:: እነዚህ አራት ራዳሮችም እያንዳንዳቸው እስከ 100 ሚሊዮን ብር ወጪ የተደረገባቸው ናቸው::

እነዚህ ራዳሮች ዝናብ ሰጪ ዳመናን በተመለከቱ ጊዜ 20 ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ሂደት (ፕሮሰስ) በማለፍ ደመና ማበልጸግ የሚቻልበትን ሂደት ያከናውናሉ:: ስራው፣ የመንግስት ትኩረት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከሌሎች አካላትም ሃብት በማፈላለግ የተከናወነ ነው:: በመሰረቱ መጀመሪያ እነዚህ ራዳሮች ሲተከሉ ዝናብን ማበልፀግ ታሳቢ በማድረግ አልነበረም:: ዋና ዓላማው የአየር ሁኔታ ማወቅን የተመለከተ ነበር:: ነገር ግን በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አነሳሽነትና ድጋፍ “ደመና ማበልፀግ” የሚለውን ሐሳብ በሰፊው አካተን ወደ ተግባር ገባን፤ አሁን እየሰራንበት እንገኛለን::

**አዲስ ዘመን፡- ቴክኖሎጂን መጠቀም እንዳለ ሆኖ የሚስጥራዊነታቸው ጉዳይ እንዴት ይታያል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ምስጢራዊነታቸውን በተመለከተ ሁሉም ቴክኖሎጂዎች የየራሳቸው ምስጢር ቁጥር አላቸው:: በዚህ ረገድ እዚህ ሲመጡ የሚስተካከሉ ነገሮች አይኖሩም ማለት አይደለም:: የተለያዩ አማራጮችን መጠቀም ይቻላል:: ነገር ግን መታወቅ ያለበት ጉዳይ የሳተላይት መረጃ ብዙም የተደበቀ ነገር የሌለው መሆኑ ነው:: እኛ ለዚህ ጉዳይ የምንጠቀመው ከፊላንድ የተገዛ ነው:: በዓለም ላይም በዋናነት አቅራቢዎች እነሱ ናቸው::

እኛም በቴክኖሎጂ ላይ ያለንን ግንዛቤ አሳድገን ለሀገር ጥቅም ብቻ እንዲውል ማድረግ ይጠበቅብናል:: ግን ምንም እንከን የለውም ማለት አይደለም:: የሚትዎሮሎጂ መረጃን በተመለከተ ደግሞ ኢትዮጵያ ያላትን ሃብትና በዓመት ምን ያክል ዝናብ ታገኛለች? ምን ያጋጥማታል? በሚሉትና ሌሎችም ላይ መረጃ ለመሰብሰብ ብዙ የሚደበቅ ነገር የለም::

ኢትዮጵያ የዓለም ሚትዎሮሎጂ ድርጅት አባል ነች:: በአባልነቷ የተለያዩ መረጃዎችን የሚሰጡ ሳተላይቶች ታገኛለች:: ሌሎች የዓለም ሚትዎሮሎጂ ድርጅት ተቋማትም የሚሰጡትን መረጃ እንጠቀማለን:: የሚትዎሮሎጂ መረጃ በአንድ ሀገር ውስጥ ብቻ የተገደበ፤ የተወሰነም አይደለም:: አንድ ሀገር የሚከሰተው ክስተት ለሌላው ሀገር መረጃ በመሆኑ ከዚህ አንጻር ዓለም አቀፍ መረጃ ልውውጥ ያስፈልጋል:: በመሆኑም ዝግ ያልሆነ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት አለ:: በመሆኑም በሚትዎሮሎጂ ላይ ያሉ መረጃዎች ያን ያክል ምስጢራዊነታቸው መጠበቁ ጠቃሚ ላይሆን ይችላል::

**አዲስ ዘመን፡- ከሀገሪቱ ቆዳ ስፋት አኳያ አሁን ያለው የሚትዎሮሎጂ መረጃ ሽፋን በቂ ነው?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ኢትዮጵያ በጣም ትልቅ ሀገር በመሆኗ የሚትዎሮሎጂ መረጃ ሽፋንን ለማሳደግ ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ ናቸው:: የሀገሪቱን ሚትዎሮሎጂ ሽፋን ለማሳደግ መረጃ የሚሰበሰብባቸውን ጣቢያዎችን የማደራጀት አጠቃላይ የጣቢያ ኔትወርክ በማሳደግ ረገድም በርካታ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ:: በአሁኑ ወቅት የሚትዎሮሎጂ መረጃ የሚሰበሰበው በሰው ኃይል ነው:: ሌላኛው በአውቶማቲክ የሚሰበሰብ ነው:: ከአየር፣ ከአውሮፕላን ላይም መረጃ ይሰበሰባል:: በተጨማሪም የአየር ሁኔታ መከታተያ ራዳር ጭምር የሚትዎሮሎጂ መረጃ እየሰበሰበ ነው:: በዚህ ደረጃ ስንት ያስፈልጋናል የሚለውን ለይተን አስቀምጠናል:: ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሚትዎሮሎጂ መረጃ በመሰብሰብ ረገድ ሰፊ ሥራ መሠራት አለበት:: ለዚህም 12 ጣቢያዎች ያስፈልጋሉ:: እነዚህ ጣቢያዎችም በተሟላ ደረጃ ወደ ሥራ ሲገቡ ሽፋኑም ሆነ ጥራቱ በዚያው ልክ ያድጋል::

**አዲስ ዘመን፡- በአደጉት ሀገራት የበረራ ሥራ በቀጥታ የሚትዎሮሎጂ መረጃ እየታገዘ ነው:: ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ምን ደረጃ ላይ ትገኛለች?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ከአየር ሁኔታ እና ጸባይ ጋር በተያያዘ ከትራንስፖርት ዘርፍ፣ በተለይም በምድር፣ በባህር ብሎም በአየር ላይ የሚንቀሳቀሱ የሚትዎሮሎጂ መረጃን በሰፊው ይጠቀማሉ:: ከእኛ አንፃር የምንሰጠው የአቬዬሽን መረጃዎችን ነው :: ከዚህ አኳያ አውሮፕላን ሲነሳ መነሻ ትንበያ እንሰጣለን:: በዚህ ምክረ ሐሳብ ከመንደርደሪያ ይነሳሉ:: ሁለተኛው በበረራ ውስጥ ያለው መረጃም ይሰጣል:: ሦስተኛ በረራ መዳረሻ ላይ መረጃዎች ይሰጣሉ:: ስለዚህ የአየር ጸባይ ጥሩ ካልሆነ በረራ ላይ ማስተካከያ ይደረጋል:: በበረራ ውስጥ የሚኖረው ደግሞ በሲቭል አቬዬሽን በኩል በአየር መቆጣጠሪያ መረጃ ይሰጣል::

> መንግስት የኢትዮጵያን የሚትዎሮሎጂ አቅም ለማሳደግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በሰፊው እየተንቀሳቀሰ ነው:: በመሆኑም ዘመኑን የዋጀ ቴክኖሎጂ እና ተቋም ስንገነባ ጎን ለጎንም የሰለጠነ የሰው ኃይል እያፈራን ነው

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት ምን ያክል ተደራሽ ሆነናል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** የተለያዩ ጣቢያዎች አሉን:: መረጃ በመሰብሰብ ረገድ አንደኛ፤ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ እና አራተኛ ደረጃ ተብለው የተከፈሉ አሉ:: በሰው መረጃ የሚሰበሰብባቸው አሉ:: ይህ በመላ ሀገሪቱ 1ሺ 300 ጣቢያዎች አሉን:: አውቶማቲክ የአየር ሁኔታ ጣቢዎችም አሉን:: ይህ በ15 ደቂቃ ልዩነት ከየትኛውም የሀገሪቱ ጫፍ የአየር ሁኔታን ወደ ሰርቨሩ ይልክልናል:: ይህም በመላ ሀገሪቱ 300 ጣቢያዎች አሉን:: ከዚህ በተጨማሪ የሳተላይት መቀበያ ማዕከላት አለን:: በተለይም ለዕጽዋት ልምላሜ፣ ለግብርናው ዘርፍ እና ለሌላ ግልጋሎትም ይውላሉ:: እነዚህንም በአዲስ አበባ ሁለት በተጨማሪ በ11 አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎቻችን ተክለን እየተጠቀምን ነው::

ብክለትን የሚከታተሉ ሳተላይቶችም እየተተከሉ ነው:: በአሁኑ ወቅት የአየር ብክለት መከታተያ ጣቢያዎችን በአዲስ አበባ፣ አዳማ እና ሃዋሳ፤ የኢንዱስትሪ መንደሮች እና የተሽከርካሪ ፍሰት በሚበዛባቸው አካባቢዎች ተክለን እየተጠቀምን ነው:: በቀጣይም ከራዳሩ ጋር እየተሠራ ባለው ፕሮጀክትም በአዲስ አበባ ውስጥ 10 የአየር ብክለት መከታተያ ጣቢያ ለመትከል ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ነው::

በአጠቃላይ ዘመናዊ የሆኑ ቴክሎጂዎችን በመጠቀም ሀገሪቱን የሚትዎሮሎጂ መረጃ ሽፋን በማሳደግ እና በቴክሎጂ በማዘመን ላይ እንገኛለን:: የሳተላይትና የጣቢያዎችን መረጃ በማዳቀል በአራት ኪሎ ሜትር ልዩነት መረጃ ለመስጠት የሚያስችል አቅም መገንባት ተችሏል:: እነዚህ መረጃዎችን በአግባቡ ከተጠቀምን ሀገሪቱ የሚትዎሮሎጂ መረጃ ሽፋንም ሆነ ተደራሽነት እያደገ የሚሄድ ይሆናል:: ይህ ዘርፍ እየተጠናከረ ሲሄድ ሌሎች መረጃ የሚፈልጉና በዋናነት በእኛ መረጃ የሚጠቀሙ ዘርፎችም በዚያው ደረጃ ያድጋሉ የሚል እምነት አለን::

**አዲስ ዘመን፡- የሚትዎሮሎጂ መረጃ ሽፋንን በጥራትና በብቃት ከማሳደግ አኳያ የመሠረተ ልማት ሥራው ምን ይመስላል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** የሚትዎሮሎጂ መረጃን ሽፋን ለማሳደግ መሠረተ ልማቱን ማሳደግ ይገባል:: ይህን ከመስራት አኳያ ደግሞ መንግስት ትልቅ ትኩረት ሰጥቷል:: በተለይም ደግሞ ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ መታጠቅ ተገቢ መሆኑ ታምኖበታል:: ከዚህ አኳያ የተለያዩ አማራጮችን በመመለከት ላይ ነን:: ከዚህም በተጨማሪ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ተቋም ለመገንባት በልዩ ትኩረት እየተሠራ ነው::

ኢትዮጵያ ከአሜሪካ እና ቻይና በመቀጠልም የሚትዎሮሎጂ መሰረተ ልማትን ሙሉ ለሙሉ አንድ ላይ የያዘ ህንፃ ግንባታ በመገንባት ላይ ናት:: ይህ ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች ያሉት ህንጻ በ1 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር እየተከናወነ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅትም የግንባታው ሂደት 73 ከመቶ ደርሷል:: በቴክኖሎጂ ረገድም ዘመናዊ የሆኑና ዘመኑ የደረሰበትን ታሳቢ ያደረጉ ናቸው::

**አዲስ ዘመን፡- ከመሠረተ ልማት ባሻገር መሰረተ ልማቱን መምራትና መቆጣጠር የሚችል የሰው ኃይል ማፍራት ተችሏል?**

**አቶ ፈጠነ፡-** የሚትዎሮሎጂ መረጃ ሽፋን እና ትንቢያን ለማሳደግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መታጠቅ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚያው መጠን ቴክሎጂውን የሚገነዘብ የሰው ኃይል ማፍራት ይገባል:: እኛም ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በርካታ ሥራዎችን በመስራት ላይ እንገኛለን:: ተቋሙን ለማዘመንና ሥራውን በፍጥነት ለማከናወን ያግዝ ዘንድም ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይል ግንባታ ጀምረናል:: ለአብነት በአሁኑ ወቅት 64 ተማሪዎች የማስተርስ፤ አምስት ደግሞ የዶክተሬት ዲግሪያቸውን በመከታተል ላይ ናቸው:: የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው በርካታ ባለሙያዎች በተቋሙ ውስጥ ይገኛሉ:: በየእርከኑና በየደረጃው የሰው ኃይል ለማብቃት በትኩረት እየተሰራ ነው::

መንግስት የኢትዮጵያን የሚትዎሮሎጂ አቅም ለማሳደግ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በሰፊው እየተንቀሳቀሰ ነው:: በመሆኑም ዘመኑን የዋጀ ቴክኖሎጂ እና ተቋም ስንገነባ ጎን ለጎንም የሰለጠነ የሰው ኃይል እያፈራን ነው:: በአስር ዓመት ስተራቴጂክ እቅዳችን እንደ ተቋም የተያዘው አቋም ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም መረጃዎችን በስፋት ለተጠቃዎች ማድረስ ነው:: ይህን ለማከናወን ደግሞ በዚያው ልክ የዘመነ የሰው ኃይል አስፈላጊ በመሆኑ በዚህ ላይ በስፋት እንሠራበታለን:: ይህ ሥራችን እየተጠናከረ ሲሄድ የሚፈለገውን ውጤት እንደምናመጣ እርግጠኞች ነን::

**አዲስ ዘመን፡- ለተቋሙ ሥራ እንቅፋት የሆኑበት ችግሮች አሉ?**

**አቶ ፈጠነ፡-** ከመጀመሪያው የነበሩብን ችግሮች እነዚህን መረጃዎችን ለማዘመን የሚያስችል አቅም መፍጠር አለመቻል ነው:: ይህ ከበጀት ጋር ይያያዛል:: ምቹ የሥራ አካባቢ አለመኖርም አንዱ ነበር:: ሰርቨሮች ሲመጡ ምቹ ማስቀመጫ ሊጠፋ ይችላል:: በቂ የኤሌክትሪክ ኃይልም አልነበረም::

በአሁኑ ወቅት እየተሟሉ ነው:: መንግስት ትኩረት በመስጠቱ ችግሮቹን በማቃለል ላይ ነን:: መሳሪያዎችን ከማዘመን አኳያ አፍሪካ ውስጥ አብዛኞቹ ሀገራት የሌላቸውን ቴክኖሎጂ እና አቅም እኛ እየገነባን ነው:: በሰው ኃይል ግንባታም በሰፊው እየሰራንበት ሲሆን ትልቅ ለውጥ እየተመዘገበ ነው:: የማዕከላትም አቅም እያደገ ነው:: ለሀገሪቱ የሚመጥን መረጃ ለመስጠት በስፋት እየሰራን ነው:: ከጉድለት ባለፈ በርካታ ጠንካራ ጎኖች ስላሉን በአሁኑ ወቅት ከመንግስት አቅም በላይ የሆነ ችግር የለም። የመንግስት ድጋፍም ከመቼውም ጊዜ በተለየ ሁኔታ የተጠናከረ ነው:: ችግሮች አሉ ብለን ብናስብ እንኳን በተቋሙ አቅም በፍጥነት መፍትሄ የሚሰጣቸው በመሆናቸው በዚህ ደረጃ ጎልተው የሚነገሩ አይደሉም::

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እያመሰገንኩ ተጨማሪ ሃሳብ፣ መልእክት ካለዎት ሊያስተላልፉ ይችላሉ።**

**አቶ ፈጠነ፡-** በጣም አመሠግናለሁ:: የኢትዮጵያ ሚትዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ዘመናዊ ቴክሎጂዎችን በመጠቀም በመላ ሀገሪቱ ተደራሽ የሆነ የሚትዎሮሎጂ መረጃ በመስጠት ላይ ይገኛል:: ኢንስቲትዩታችን ዛሬ ከሚሰጠው አጠቃላይ የበልግ ትንበያ በተጨማሪ በመጪው በልግ መካከል በሀገራችን የተለያዩ ቦታዎች ሊፈጠሩ የሚችሉትን የአየር ሁኔታ ገፅታዎችን አስቀድሞ በመተንበይ የቅድመ-ማስጠንቀቂያ እና የትንበያ መግለጫዎችን የሚሰጥ በመሆኑ ኅብረተሰቡ ይህንኑ መረጃ ቢጠቀም የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ::

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# “ግዛዋ ሳለ ከደጅሽ፤ ለምን ሞተ ልጅሽ!?”

## ነገረ ግዛዋ - የመነሻ ወግ፤

ለመድኃኒትነት ከሚውሉ በርካታ ሀገር በቀል ዕፅዋት መካከል አንዱ ግዛዋ ነው።በአንዳንድ አካባቢዎች ግዛዋ የሚታወቀው “ጊዜዋ” እየተባለ ነው።በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎችም የተለያዩ ስያሜዎች እንዳሉት አንብቤያለሁ።ግዛዋ የትም የሚበቅል ገርና ገራሚ ዕፅ ነው።በግቢ ውስጥ፣ በመስክ ላይ፣ በሸለቆና በተራራ ሳይቀር ሁሌም ወቅት ሳይጠብቅ እንደለመለመ አምሮበት መታየቱ የተለመደ ተፈጥሮው ነው፡፡

እንደ ጓደኞቹ እንደ እነ ዳማከሴ፣ ድንገተኛ፣ ቀበርቾ፣ ፌጦ፣ ኮሶ ወዘተ. “ራሱን በማዋደድ” ርቃችሁ በመጓዝ ፈልጉኝ፣ አጠያይቃችሁ አግኙን በማለት “የሚኮፈስ” ዕፅ አይደለም።የትም ይበቅላል፤ በቀላሉም ይገኛል።ይህ ግዛዋ ዘርፈ ብዙ የመድኃኒትነት ጥቅም ይሰጣሉ ከሚባሉ ሁሉ ገብ መድኃኒቶች መካከል የሚጠቀሰው በሀገር በቀል ዕውቀቶች ብቻ ተመስክሮለት ሳይሆን በሳይንስ የምርምር ዘርፎችም እውቅናን በማግኘቱ ጭምር ነው።የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት በማኅበራዊ ድረ- ገጹ ላይ ያሠፈራቸው የጥናት ውጤቶች የሚጠቁሙትም ይህንኑ እውነታ ነው፡፡

በሳይንሳዊ ስሙ ዊታኒያ ሶምኒፌራ (Withania Somnifera) በእንግሊዘኛ ስያሜው Winter Chery በመባል የሚታወቀው የሀገሬ ግዛዋ ለራሱ ባለሀገሮች ባዕድ ሆኖ ቢታይም በሌሎች የዓለም ሀገራት ዘንድ ግን ተከብሮና ተመስግኖ በሳይንስና ምርምር እየተፈተነ በፈሳሽና በጥጥር መልኩ በፋብሪካዎች ውስጥ በመመረተ የደዌ ከልነቱን ተልዕኮ በሚገባ በመወጣት ላይ ይገኛል።በእኛው ቀዬ ግን “ከሞኝ ደጅ ሞፈር መቆረጡ” ወግና ባህላችንም አይደል፡፡

በተለየ ሁኔታ በህንዶች ዘንድ አሽዋጋንዳ (Ashwagandha) በሚል ስያሜ ዝናን የተጎናጸፈው ይህ ተክል “የመታወቂያ” ስሙን ያገኘው እንደ ፈረስ ጉልበታማ የሆነ መዓዛማ ሽታ ያለው ሁለገብ ፈዋሽ (Horsey Smell) እየተባለ ነው።ምንም እንኳን ይሄው ገራሚ የዕፅዋት ዝርያ በበርካታ የአፍሪካ፣ የሰሜን አሜሪካና የእስያ ሀገራት በስፋት ቢገኝም ህንዶች የተጠቀሙበትን ያህል የትኛውም ሀገር ተግባር ላይ እንዳላዋለው በበርካታ ጥናቶች ውስጥ ተጠቅሷል፡፡

ዕፁ ለየትኞቹ የጤና ችግሮች መፍትሔ እንደሚሰጥ ለመተንተን ጸሐፊውም ሆነ ይህ ጽሑፍ የዕውቀት ሥልጣንም ሆነ ብቃት (Authority) የላቸውም።በአንዳንድ ጽሑፎች ውስጥ እንደተጠቀሰው ግን ለአእምሮ ህመም፣ ለጭንቀት፣ ለድብርት፣ የጡንቻን ብቃት ለመታደግ፣ የልብን ምት ለማስተካከል፣ የቆሰለን አካል ደም ለማስቆም እና ለሌሎች በርካታ ደዌዎች በተጠናና በተስተካከለ ምጣኔ ጥቅም ላይ ከዋለ በፈዋሽነቱ ላይ ጥርጣሬ እንደማይኖር የዘርፉ ተመራማሪዎች መጠቋቆማቸው አልቀረም።ይህ አምደኛ የግዛዋን ዕፅ ለጽሑፉ ማዋዣ እንዲሆን የመረጠው የጽሑፉን ዋና ይዘት ያብራራ እንደሆን ብሎ በማሰብ እንጂ በዕፁ ላይ እንደ ተመራማሪ ሊቆጠርና ለዕፁ ፈዋሽነትም ማረጋገጫ እንደሰጠ ሊቆጠር እንደማይገባ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

ወደ መነሻው ጉዳያችን እናቅናና የልጇን ህመም እንደ አዘቦት ቀናት የጤና ማጣት በመቁጠር ቸል ያለችን አንዲት እናት በደጃፏ ተንዠርግጎ ካለው ከዚህን መሰሉ የግዛዋ ተክል ሸምጥጣ ልጇን መታደግ ተስኗት በቸልተኝነት በሞት መነጠቁን ለማመልከትና ለመገሰጽ ስለተፈለገ ይመስላል፡- “ግዛዋ ሳለ ከደጅሽ፤ ለምን ሞተ ልጅሽ” ተብሎ ተተረተ ይባላል።“ግዛዋ ሞልቶ ከዱርሽ፤ ምነው ሞተ ልጅሽ” እየተባለም ይተረታል፡፡

## ኢትዮጵያ ሆይ! - እውቀት እያለ ከደጅሽ፤ ስለምን ሞቱ ልጆችሽ?

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እንደ ሀገር የተፈተንባቸውን ሀገራዊ ቀውሶች እንደ መነሻ በማስታወስ ብቻ እየፈከርን ለገደልናቸው ወይንም ላስገደልናቸው፣ እያነባን ለቀበርናቸው ወይንም ወግ ያለው ቀብር እንኳን አጥተው ለአራዊት ሲሳይ ለሆኑት ሙታን ዜጎቻችን “ሀገራዊ የሕዝብ ቆጠራ” እንዲሉ፤ በጦርነትም ሆነ በበርካታ ማሕበራዊ ቀውሶች መንስዔ ደማቸው ደመ ከልብ ሆኖ በከንቱ ወድቀው ለቀሩት ኢትዮጵያዊያን በዝክረ ሙታን ስያሜ የመስዋዕትነት ቆጠራ (“crude` national census) ቢደረግ የአሀዙ ውጤት ምን ያህል ሚሊዮን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት ሳያዳግት አይቀርም፡፡

> ለሰላም ንግግርና ምክክር በየቋያችን ከስሩ የምንጠለልበት ለምለም የዋርካ ዛፍ እያለን፣ “በግዛዋ” የምንመስላቸው አፈርሳታና አውጫጭኝ ባህልና ወጋችን ሆነው እያሉ ስለምን ልጆቻችን በከንቱ እንዲያልቁ እንፈርድባቸዋለን?

በምሳሌ እናብራራው፡- የጦርነት መዘዝ ያስከተለብን ጥቁር መጋረጃ ለጊዜው እንደተዘጋ በይደር ይተላለፍና ዘርህ ከዘሬ አልተቀዳም፣ ቋንቋህ ከቋንቋዬ አይገጥምም፣ ብሔርህ ከብሔሬ ያነሰ ነው፣ ባህልህ ባህሌ አይደለም፣ ወግህም ከወጌ አይዛመድም በሚል እብሪትና ትምክህት ስንት ንፁሐን ዜጎቻችን እንደረገፉብን ምስክሩ ፀባዖት ብቻ ነው።ሃይማኖቴ ለሃይማኖትህ ባላንጣ ነው፣ እምነቴ ለእምነትህ ባዕድ ነው፣ ዶግማህ ዶግማዬን ተጻይፎታል፣ ቀኖናህም ለቀኖናዬ ፀር ነው በሚል ምክንያትና ሰበብ የምን ያህሉ ወገን እስትንፋስ እንደጨለመ፣ ምን ያህሉ ወገንም ሳይታወቅለት እንዳለፈ ምስክር ልትሰጥ የምትችለው ይህቺ እንደ ጉድ የደም አበላ የጠገበችው “አኬልዳማችን” ኢትዮጵያ ብቻ ነች፡፡

በታሪክ ትንታኔና አረዳድ መግባባት ተስኖን በተለኮሰ የእሳት ወላፈን ምን ያህሉ ወገን እንደ ቅጠል እንደረገፈ፣ ምን ያህሉ ዜጋ በማያውቀውና በማይገባው የፖለቲካ ወፈፌዎች የእሳት ራት እንደሆነ ዝርዝሩ የሚገለጥልን ወደ ቀልባችን ተመልሰን ከደም ፍላት ስንቀዘቅዝ ወይንም ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚያስተምረን በመጨረሻው የፍርድ ቀን የእያንዳንዳችን ግለ ፋይል በፈራጁ አምላክ ፊት ሲገለጥ ብቻ ይሆናል፡፡

ይህን መሰሉ በሀገሪቱ ላይ እየደረሰ ያለው መከራና አሳር ያነሰን ይመስል በሰንደቅ ዓላማ ቀለምና ትርጉም፣ የትኛው ከፍ ብሎ ይውለብለብ፣ ወዘተ. በሚሉ ሰንካላ ምክንያቶች የተነሳ ምን ያህሉን ነፍስ እንደገበርን ለምን ያህሉ ዜጎች የሥነ ልቦና ቀውስ እንደዳረግን ዛሬ አድበስብሰን ብናልፍ ነግ ተነገ ወዲያ እውነታው በፀሐይ ፊትና በአደባባይ ላይ መሰጣቱ አይቀርም፡፡

ለመሆኑ በሚያግባቡን ተግባብተን፣ በማያግባቡን ተቀባብለን እንዳንኖር አዚም ያደረገብን ምድራዊ ወይንም መንፈሳዊ ኃይል ምን ይሆን? በሥጋዊ ጡንቻችን ሳይቀር እስከ መፋለም ያዙኝ ልቀቁኝ እያልን ለያዥ ለገራዥ ያስቸገርነው በርግጡ የልብ ልብ የሰጠን ትምክህት ምንጬ ምን ይሆን?

ለሰላም ንግግርና ምክክር በየቋያችን ከስሩ የምንጠለልበት ለምለም የዋርካ ዛፍ እያለን፣ “በግዛዋ” የምንመስላቸው አፈርሳታና አውጫጭኝ ባህልና ወጋችን ሆነው እያሉ ስለምን ልጆቻችን በከንቱ እንዲያልቁ እንፈርድባቸዋለን? ስለምንስ የፖለቲካ አታካራዎቻችንን በመነጋገር መፍታት እየተቻለ “ደም ሳይፈስ ሥርዬት የለም” በሚል ብሉያዊ ፍልስፍናና እምነት ታብተን ለመጠፋፋት እንጨካከናለን? በቁጭት ወርዝቶ ከውስጣችን የሚገነፍለው የጥያቄ ወጨፎ ስፍር ቁጥር ስለሌለው እንዲሁ ብቻ ነካክተነው ማለፉ ይበጃል፡፡

ለመሆኑ እንደ እኛ እንደ ኢትዮጵያውያን የፈጣሪን ስም በአንደበቱ ሲያመነዥክ ውሎ የሚያድር ሌላ ሕዝብ ይኖር ይሆን? እንዴት አደርክ/ሽ ሲባል እግዚአብሔር ይመስገን የሚል፣ በጎ ሲደረግለት እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብሎ የሚመርቅ፣ ስናቅድ እግዚአብሔር ቢፈቅድ የምንል፣ በህመማችን ወቅት እግዚአብሔር ይማርሽ/ህ ተባብለን የምንጽናና፣ “ስለ እግዚአብሔር ብለህ/ሽ” እየተባባልን ለእርቅ የምንፈቃቀድ፣ “ኢንሽ አላህ” እያልን በቅዱስ ቁርዓን ውስጥ 2699 ያህል ጊዜያት የተጠቀሰውን የፈጣሪ ስም የዚያኑ ያህል በቀን ውስጥ በማንሳትና በመጣል ስንጠራ እየዋልን ስለምን መከባበርና መቀባበል ተሳነን?

ጠይቀንና ተጠያይቀን መልስ ከማናገኝላቸውና መልሱ ባይገኝም ደጋግመን መጠየቅን የማናቆምባቸው ሀገራዊ ጉዳዮቻችንና ችግሮቻችን ብዙዎች ናቸው።ብሶት የሚወልዳቸው ችግሮቻችን ገንፍለው ያልተፈለገ ውጤት ከማስከተላቸው አስቀድሞ በሆደ ሰፊነትና በትክክሻ ደንዳናነት ተሰባስበን በጥያቄዎቻችንና በፈተናዎቻችን ዙሪያ መፍትሔውን በጋራ ለመፈለግ ዝግጁ እስካልሆንን ድረስ ሥር የሰደደው በሽታችን በነጋ በጠባ እያገረሸ ስናቃስት መኖራችን ግድ መሆኑ አይቀሬ ነው።

አድምጠኝ ላድምጥህ ከመባባል ይልቅ ሻምላ ተማዝን ይለይልን ተባብሎ የደም ሸማ መጣጣሉ የት እንዳደረሰን ስለሚታወቅ ቆም ብለን ልናስብበት ይገባል።ችግሮቻችንን “ድፍን ዕንቁላል” እንደሆነ በማሰብ “ዕንቆቅልሾቻችን” ማወሳሰቡ የት አድርሶ ምን ላይ እንደሚጥለን ቆም ብለን ካላሰብን በስተቀር የእብሪትና የትምክህት ሽክርክሪያችን አዙሮ የሚዘፍቀን ወደ ደም መፋሰስ መሆኑ በጥብቅ ሊታሰብበት ይገባል።ችግሮችን በንግግር መፍታት እየተቻለ ገድሎና ተጋድሎ ያሸነፈ፣ ነፍሱም ተከብራ ኒሻን የተሸለመች “ጻድቅ” ጥንትም ሆነ ዛሬ ኖሮ አያውቅም፤ ለወደፊቱም ይኖራል ተብሎ አይታመንም፡፡

ጠነንና ኮስተር ያለውን ይህንን ጨፍጋጋ ርዕሰ ጉዳይ የሚያለዝብልንን አንድ ሰሞንኛ ዓለም አቀፍ አወዛጋቢ ክስተት ለማዋዣነት እንጥቀስ።ከህንድ የተገኘውን ይህንን የቀደሙን ዜና ተሽቀዳድሞ ለዓለም ያዳረሰው CNN የተባለው አነፍናፊ ሚዲያ ነው።የዜናውን ይዘት እንደሚከተለው አሳጥረን እንጠቅሳለን፡፡

ከህንድ ዜጎች 80% ወይንም 1.3 ቢሊዮን ቁጥር ያላቸው የሂንዱ ጎሳ አባላት ላሞችን የሚመለከቱት እንደ ቅዱስ ፍጡር ስለሆነ አያንሳቁሏቸውም፣ አያርዷቸውም፣ ተዳፍረው እንኳን ቢነኳቸው ለራሳቸው እንዳይረክሱና ላሞቹንም እንዳያረክሷቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋሉ።ብዙው ድርጊታቸው አነጋጋሪና አወዛጋቢ ስለሆነ ሁሉንም በዝርዝር መተንተኑ እጅግም አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡

ትናንት ፌብሯሪ 14 (የካቲት 7) ብዙ ምእራባዊያን ሀገራት የሚያከብሩት የቅዱስ ቫለንታይኑ የፍቅረኞች ቀን በሂንዱዎችም ዘንድ የተከበረው አነጋጋሪ በሆኑ ትዕይንቶች ታጅቦ ነበር።አስገራሚ የተባለለት ይህ የፍቅረኞች ቀን ሲዘከር የዋለው “ከላሞች ጋር በመተቃቀፍ” (Cow hug Day) የሚል መንግሥታዊ ትዕዛዝና መመሪያ ተሰጥቶበት ጭምር ነበር።ይህ መንግሥታዊ መመሪያ ምንም እንኳን በበርካታ የሀገሪቱ ዜጎች ተቃውሞና ትችት ማስተናገዱ ባይቀርም ውሳኔውና ድርጊቱ ግን አንዳች ትምህርት ሳያስተምር አላለፈም፡፡

የሰው ልጅ እንኳንስ በፈጣሪ አምሳል ከተፈጠረው የራሱ ወገን ጋር ቀርቶ ለእንስሳት እንኳን ሳይቀር ከላይ እንደተጠቀሰው “ቅዱስነታቸውን አምኖ” ፍቅሩንና አክብሮቱን ይገልጽላቸዋል።አላግባብም ይሁን በመዳፈር የእንስሳቱን ደም በከንቱ ሊያፈስ ቀርቶ ጠንከር አድርጎ እንኳን ልምጭ አያሳርፍባቸውም።ለቤት እንስሳት ብቻም ሳይሆን ለዱር አራዊትም ሳይቀር “እንስሳዊ መብታቸው” እንዲከበርላቸው “በሕግ አምላክ!” እያሉ የሚሟገቱላቸው ግለሰቦችና ተቋማት ቁጥር ልክና መጠን የለውም፡፡

የእኛ ሀገሩ የሰው ለሰው ጭካኔ ግን ስለምን ከእንስሳት ፍቅር እንኳን አንሶ እርስ በእርስ መገዳደልን ለመጠየፍ እንዳልቻልን ራሳችንን በራሳችን ልንሞግት ይገባል።እርቅ፣ ሽምግልና፣ መነጋገር፣ መወያየት፣ አፈርሳታ፣ አውጫጭኝ ወዘተ. የመሳሰሉና በሀገር በቀል ግዛዋ የሚመሰሉ የሰላም መፍጠሪያና መነጋገሪያ ባህላዊና አካባቢያዊ መድረኮች የሺህ ዘመናት ባህሎቻችን ሆነው እያሉ “ልጆቻችን ሲገዳደሉ እንዴት ዝም ብለን ለማስተዋል የሞራል አቅም አገኘን? ገሎ ማቅራራትስ ስለምን የቁራኛ ያህል ተጣብቶን ባህላችን እስከ መሆን ደረሰ? ።

”የፖለቲካ፣ የብሔርም ሆነ የሃይማኖት ምክንያት እየተሰጠው ኮሽ ባለ ቁጥር ገሎ ለመሞት መሽቀዳደሙ በርግጡ ርእዮተ ዓለማዊ ወለድ ችግር ብቻ ነው ወይንስ ውስጣችን ያልተፈወሰበትና “ግዛዋ” የምንፈልግበት ሥር የሰደደ የሀገራዊ ህመማችን በሽታ ይሆን?” - ኢትዮጵያ ሆይ! አባባሉን ለዛሬው ዐውዳችን እንዋሰውና፤ “ማግባባት ሲቻልሽ በጓዳሽ፤ ስለምን ይተላለቃሉ ልጆችሽ!?” ፈጣሪ አምላክ ድንጋዩን ልባችንን ወደ ሥጋ ልብ ይለውጥልን፤ አሜን! ሰላም ለሕዝባችን፤ በጎ ፈቃድም ለዜጎች!

# ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ገበያን የማረጋጋት ተግባር

**ፍሬሕይወት አወቀ**

በሀገሪቱ እየተባባሰ የመጣውን የዋጋ ጭማሪ ለማረጋጋት መንግሥት የተለያዩ አማራጮችን ሲወስድ ይታያል:: ገበያን ለማረጋጋት መንግሥት ከወሰዳቸውና እየወሰዳቸው ከሚገኙ እርምጃዎች መካከል የግብርና እንዲሁም የኢንዱስትሪ ምርቶችን በኅብረት ሥራ ማኅበራት አማካኝነት በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ተደራሽ ማድረግ አንዱ ነው::

አምራችንና ሸማቹን በቀጥታ በማገናኘት ጤናማ የግብይት ሥርዓት ለመፍጠር የባዛርና የኤግዚቢሽን ገበያ ወሳኝ እንደመሆኑ የባዛርና የኤግዚቢሽን ገበያ በተለያየ ጊዜ ይዘጋጃል:: በገበያውም ሸማቹ ከአምራች አርሶ አደሮችና ከኅብረት ሥራ ማኅበራት ጋር በቀጥታ የሚገናኝበት ሰፊ ዕድል ይፈጠራል:: ይህም ሸማቹ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት ያስችለዋል:: በኅብረት ሥራ ማኅበራት በኩል በተለያየ ጊዜ ባዛርና ኤግዚቢሽኖች የሚዘጋጁት በዚሁ ምክንያት ነው::

እነዚህ ማኅበራት በተለይ በከተሞች ገበያን በማረጋጋት በኩል ትልቅ ድርሻ አላቸው:: በከተሞች አካባቢ የሚስተዋለውን የምርት እጥረትና የሸቀጦች ዋጋ ንረት ለማረጋጋት ሚናቸው የጎላ ነው:: ማኅበራቱ ከመቼውም ጊዜ በተለየ  በአሁኑ ወቅት የኑሮ ውድነቱን መቋቋም እንዲቻልና ገበያውን ለማረጋጋት የድርሻቸውን እየተወጡ ይገኛሉ::

በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ከየካቲት 2 እስከ 6 ቀን 2015 ዓ.ም የተካሄደው ሁለተኛው ከተማ አቀፍ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኤግዚቢሽንና ሲምፖዚየም ገበያን ለማረጋጋት ከተዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች አንዱ ነው:: ኤግዚቢሽንና ሲምፖዚየሙ ‹‹የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለአገር እድገት መሠረት ናቸው›› በሚል መሪ ቃል ነው የተካሄደው::

እኛም በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ተገኝተን ገበያውን ቃኝተናል:: በሁለተኛው ከተማ አቀፍ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ በርካታ የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች ለገበያ ቀርበዋል:: ገበያው እንዳለፉት ተመሳሳይ ገበያዎች ሞቅ ደመቅ ያለ ባይሆንም፣ ሸማቹ በኤግዚቢሽን ባዛሩ ያገኘውን ምርት ከየዓይነቱ ሲሸምት አስተውለናል:: ሸማቹንና አምራቹን በማነጋገርም ሀሳባቸውን ተጋርተናል::

በኤግዚቢሽንና ባዛር ገበያው ሲሸምቱ ካገኘናቸው ሸማቾች መካከል ወይዘሮ መሠረት አሳዬ አንዷ ናቸው:: ከሃና ማርያም አካባቢ መምጣታቸውን የተናገሩት ወይዘሮ መሠረት፣ እንዲህ ዓይነት ገበያ ለሸማቹ ማኅበረሰብ እጅግ በጣም ጥሩ እንደሆነና ገበያውን የማረጋጋት ዕድል እንደሚፈጥርም ይገልጻሉ::

እሳቸውም በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ የተለያየ ዓይነት ምርቶች ቀርበዋል ይላሉ:: ምርቶቹ ግን በሚፈለገው መጠን በስፋት አልገቡም ነው የሚሉት:: ያም ቢሆን ታዲያ እርሳቸው ከሚኖሩበት አካባቢና በአጠቃላይ ውጭ ካለው ገበያ አንጻር ገበያው የተሻለ ሆኖ አግኝተውታል፤ በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመትም ችለዋል::

እሳቸው እንዳሉት አንድ ኪሎ ጤፍ በአካባቢያቸው ከ70 እስከ 75 ብር የሚሸጥ ሲሆን በኤግዚቢሽን ባዛሩ በ51 ብር መግዛት ችለዋል:: በዚህም በአንድ ኩንታል ከ800 እስከ 900 ብር ድረስ ቅናሽ ማግኘት እንደቻሉ ነው ያስረዱት::

ከጤፍ በተጨማሪ ገብስ እና የሽሮ እህል የሆነውን አተርና ሽንብራ ጭምር መግዛታቸውን የጠቀሱት ወይዘሮ መሠረት፤ ዋጋውም ውጭ ካለው ቅናሽ መሆኑን ተናግረዋል:: ለአብነትም አንድ ኪሎ ገብስ ውጭ ባለው ገበያ ከ50 ብር በላይ እንደሆነ ጠቅሰው፣ በኤግዚቢሽን ባዛሩ ግን አንድ ኪሎ ገብስ በ35 ብር መሸመት ችለዋል:: የሽሮ አተርን በተመለከተም ውጭ ላይ 100 ብር እና ከ100 ብር በላይ የሚሸጠውን እርሳቸው በ80 ብር መግዛት እንደቻሉ ነው የገለጹት::

ሸማቹ እንዲህ አይነት የገበያ አማራጮች ሲቀርቡለት ከየአካባቢው መጥቶ መግዛት ቢችል ተጠቃሚ ይሆናል ይላሉ:: ‹‹እንዲህ አይነት ገበያ በቀጣይም ተጠናክሮ ቢቀጥል ጥሩ ነው›› የሚሉት ወይዘሮ መሠረት፤ ከተለያየ አካባቢ ለሚመጣው ሸማች ቦታው ርቀት ቢኖረውም ካለው የዋጋ ልዩነት አንጻር አዋጭ መሆኑን ይገልጻሉ::



ከንቲባ አዳነች አቤቤ ኤግዚቢሽንና ባዛሩን በከፈቱበት ወቅት

ገበያን በማረጋጋትና የኑሮ ጫናውን በማቃለል በጎ ተጽዕኖ ያላቸው እንዲህ አይነት የገበያ አማራጮችን በማስፋት አምራቹ ከሸማቹ ጋር በቀጥታ ተገናኝቶ መሸመት ቢችል መልካም ነው በማለት ሀሳባቸውን ቋጭተዋል::

ሌላኛው አስተያየት ሰጪ አቶ ታምራት መንገሻ እንዳሉት፤ ገበያው ብዙም አጥጋቢ አይደለም:: ለዚህም ምክንያቱ በኤግዚቢሽን ባዛሩ በስፋት የሚታዩት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የተቋቋሙ የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መሆናቸው ነው:: እነሱ ደግሞ በመኖሪያ አካባቢዎች በየቀበሌው የሚገኙ ናቸው:: ዋጋቸውም ተመሳሳይ ነው ይላሉ::

ከዚህ ቀደም እንዲህ ባለ ኤግዚቢሽንና ባዛር በሀገሪቷ ከሚገኙ የተለያዩ ክልሎች የሚመጡ አምራቾች ይሳተፉ እንደነበር በማስታወስ፤ ከጎጃም፣ ከደብረብርሃን፣ ከኦሮሚያ ክልልና ከሌሎች አካባቢዎችም ይመጡ እንደነበር ያስታውሳሉ::  አሁን ግን ከየረርና በቾ ብቻ የመጡ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ገበያው እንደዚህ ቀደሙ ሞቅ ያለ አይደለም ብለዋል:: በዚህ የተነሳም ውጭ ካለው ገበያ ብዙም የተለየ ነገር እንዳላገኙም ነው የተናገሩት::

ከዚህ ቀደም በዚሁ ኤግዚቢሽንና ባዛር የከፋ ጫካ ቡና፣ የሐረርና ሌሎች ምርቶችም በቀጥታ ገበሬው ይዞ ይቀርብ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ታምራት፤ በዚህ ገበያ ግን ብዙም እንዳልተደሰቱ ተናግረዋል:: አምስት ሊትር ዘይት በ880 ብር እንደገዙና በአካባቢያቸው በሚገኝ የሸማች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ሱቆችም በ880 ብር አምስት ሊትር ዘይት እንደሚሸጥ ተናግረዋል::

አቶ ታምራት በርካታ ምርቶች ከየክልሉ እንዳልመጡ ጠቅሰው፣ በጤፍ ምርት አቅርቦትና ዋጋ ላይ ግን የተሻለ ነገር እንዳለ ነው የተናገሩት:: አንድ ኪሎ ጤፍ ውጭ ላይ እስከ 70 ብር እየተሸጠ ባለበት በዚህ ወቅት በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ከ51 ብር እስከ 57 ብር በኪሎ እየተሸጠ መሆኑን ገልጸዋል:: ይህም ገበያውን ማረጋጋት እንደሚችል በመግለጽ የወይዘሮ መሠረት ሃሳብን ደግፈው ተናግረዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ ከነጋዴው በተሻለ ዋጋ የሚያቀርቡ ቢሆንም እንዲህ አይነት ገበያ ላይ አምራቾች ከክልሎች መምጣት እንደነበረባቸው ያመለክታሉ:: ከዚህ ቀደም የዛሬ ሁለትና ሦስት ዓመታት በርካታ አምራች አርሶ አደሮች ከየክልሎቹ ይመጡ እንደነበርም አስታውሰው፣ አርሶ አደሮቹ በዚህ ላይ መጥተው ቢሆን በተሻለ መጠን እንዲሁም በተመጣጣኝ ዋጋ መሸመት ይቻል እንደነበር ነው ያስረዱት::

በኤግዚቢሽንና ባዛሩ የግብርና ምርቶችን ይዘው ከቀረቡት የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየኖች መካከል የደቡብ ክልል መሊቅ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ዩኒየን አንዱ ነው:: የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባዘጋጀው የሁለተኛው ከተማ አቀፍ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ መገኘታቸው ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የዩኒየኑ የግብይት ባለሙያ አቶ ዲንሰፉ ሽኩር ይናገራሉ::

እሳቸው እንዳሉት፤ ዩኒየኑ የተለያዩ ጥራጥሬዎችንና የእህል ምርቶችን ይዞ መቅረቡን ገልጸው፤ ለአብነትም በቆሎ፣ ባቄላ፣ አተር ገብስና የገብስ ቅንጬ እንዲሁም በቆሎና የበቆሎ ቅንጬ ለገበያ ማቅረቡን ያብራራሉ:: ምርቶቹን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ከማቅረብ ባለፈ እንዲህ ባሉ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች መሳተፍ የተለያዩ ጠቀሜታዎች እንዳሉት አስረድተዋል:: ለአብነትም ዩኒየናቸው ከተለያዩ ዩኒየኖች እና ሸማቾች ጋር የገበያ ትስስር መፍጠር መቻሉን ጠቁመዋል::

ወደ ገበያው ይዞ የቀረባቸውን ምርቶችም በስፋት መሸጥና እነሱ ካሉበት ቦታ ድረስ ሄደው ሊገዙ የሚችሉ የተለያዩ ተቋማትን ማግኘት እንደቻሉና የገበያ ትስስር የመፍጠር ዕድል እንዳገኙም ተናግረዋል:: አምራቾች እርስ በእርስ የመተዋወቅ እድል የፈጠረላቸው መሆኑን የገለጹት አቶ ዲንሰፉ፤ የትኛው ምርት ማን ጋ እንዳለና እንደሌለ የመለየት ሰፊ ሥራ የተሠራ መሆኑንም ተናግረዋል::

እንዲህ ዓይነት ኤግዚቢሽንና ባዛር ገበያ ማረጋጋትና የኑሮ ውድነቱን ማቃለል ዋንኛ ዓላማው ነው ያሉት አቶ ዲንሰፉ፤ ገበያን ለማረጋጋት ከዚህ የተሻለ አማራጭ እንደሌለም ነው የሚገልጹት:: ይህን አይነቱ ባዛርና ኤግዚቢሽን ዋጋና ገበያን ማረጋጋት ዓላማ አድርጎ እንደሚዘጋጅ ጠቅሰው፣ በቀረበው ምርት ሸማቹ ተጠቃሚ እንደሚሆን ይገልጻሉ:: ለአንድና ለሁለት ወራት ቢሆንም ለሸማቹ አስቤዛ መሸመት የሚችልበትን ዕድል ለሸማቹ ፈጥሮለታል ይላሉ:: በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ አምራቹ በስፋት ባይገባም፣ በርካታ ቁጥር ያላቸው የሸማች ኅብረት ሥራ ማኅበራት መገኘታቸውን ግን ገልጸዋል::

ዩኒየኑ 192 አባል ማኅበራትና 105 ሺ የተናጠል አባል አርሶ አደሮች ያሉትና ሰፊ እንቅስቃሴ እያደረገ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ዲንሰፉ፤ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ለአርሶ አደሩ ምርጥ ዘርና የአፈር ማዳበሪያ ያቀርባል ብለዋል:: በዚህም ጥራት ያላቸውን የግብርና ምርቶች ተቀብሎ በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ ያቀርባል:: በቀጣይም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጥራት ያላቸውን ምርቶች ለማምረት በርካታ ሥራዎችን እንደሚሠራም ይናገራሉ:: በተለይም አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ ከአርሶ አደሩ ጋር እጅና ጓንት ሆኖ ይሠራል ብለዋል::

ሌላው በኤግዚቢሽን ባዛር ያገኘነው የኦሮሚያ የግብርና ኅብረት ሥራ ማኅበራት ፌዴሬሽን ነው:: ፌዴሬሽኑ የፋብሪካ ውጤት ምርቶችን ይዞ ነው የቀረበው:: የፌዴሬሽኑ የገበያ ባለሙያ አቶ አሸናፊ ፈይው እንዳሉት፤ ፌዴሬሽኑ የግብርና እንዲሁም የፋብሪካ ውጤቶችን ያመርታል:: በአሁኑ ወቅትም የፋብሪካ ምርቶች የሆኑ የበቆሎ ዱቄት፣ የበቆሎ ቅንጬ፣ ለከብቶች መኖ የሚሆን የበቆሎ ተረፈ ምርት ይዞ ቀርቧል:: ምርቶቹም በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች በሚገኙ ሱቆች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፤ በእሁድ ገበያ ላይም ተሳታፊ በመሆን ተደራሽ ናቸው::

ከዚህ በተጨማሪም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ናሙናዎችን ይዘው መቅረባቸውን ያነሱት አቶ አሸናፊ፤ ሽንብራ፣ ማሾ፣ ቀይ ቦሎቄ፣ ነጭ ቦሎቄና ዥንጉርጉር ቦለቄን ለማሳያነት ይዘው መቅረባቸውን ነው የተናገሩት:: እነዚህ ምርቶች ከአርሶ አደሩ የሚሰበሰቡና ወደ ውጭ ገበያ የሚላኩ እንደሆኑም ተናግረዋል::

አርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ እንዲችል የተለያዩ ድጋፎች ይደረጉለታል ያሉት አቶ አሸናፊ፤ በተለይም ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ላይ ከፍተኛ እገዛ የሚደረግላቸው መሆኑን አመላክተዋል:: ለአብነትም ፀረ-ተባይ ምርቶችን ከውጭ በማስመጣት ለአርሶ አደሩ በተመጣጣኝ ዋጋ ይከፋፈላል:: ከዚህ በተጨማሪም የትምህርት ቁሳቁስን ከውጭ በማስመጣት አባል ለሆኑ አርሶ አደር ቤተሰቦች በተመጣጣኝ ዋጋ ተደራሽ ያደርጋል ብለዋል::

በመክፈቻ ሥነሥርዓቱ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አበቤ፤ ‹‹የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ማጠናከር ኅብረተሰብን መደገፍ ነው›› በማለት የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ በሀገር ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚኖራቸው አስተዋጽኦ የጎላ መሆኑን አስታውቀዋል:: በተለይም ማኅበራቱ ሰው ሠራሽ የሆነውን የኑሮ ውድነት በማቃለል የግብይት ሰንሰለቱን በማሳጠር ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳላቸው ተናግረዋል::

በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ ከ170 በላይ የኅብረት ሥራ ማኅበራት መገኘታቸውንና ከ10 ሺ በላይ ኩንታል የሰብል እህል መቅረቡን መረጃዎች ያሳያሉ:: ማኅበራቱ አምራቾችን እና ሸማቾችን በማገናኘት ካላቸው የላቀ ሚና ባሻገር የኑሮ ጫናውን ከማቃለል አንጻር ጉልህ ድርሻ አላቸውም ተብሏል::

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## «ደረሰኝ ሳይቀበሉ ሒሳብ ይክፈሉ»

**ዋስልኝ አየለ**

የጥምቀት ዕለት ማታ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ላምበረት አካባቢ የሚገኝ አንድ ሥጋ ቤት ገባን:: ቤቱ አዲስ ይመስላል፤ እዚያ አካባቢ ብዙ ጊዜ ተንቀሳቅሼ ስለማውቅ ከዚያ በፊት ብዙም አይቼው አላውቅም::

ለማንኛውም ከዚህ ቤት ገብተን ምግብ አዘዝን:: ማወራረጃውንም ተጠቀምን:: በመጨረሻም አስተናጋጇን ሒሳብ ስሪልን አልናት:: ደረሰኝ ስንጠብቅ መጥታ ሒሳቡን ነገረችን::

ሒሳቡ በጣም የተጋነነ ሆነብን፤ ከሰጠናት በኋላ ‹‹ይህኛው ይህን ያህል ቢሆን፣ ይህኛው ይህን ያህል...›› እያልን የተጠቀምነውን ደመርነው:: ሌላ ቦታ ከምናውቀው ጋር አነፃፅረን ስንደምረው ከከፈልነው ሒሳብ ጋር ተራራቀ፤ ቤቱም ያን ያህል የተለየ የሚባል አይደለም:: እኔ አንዴ ሆኗል ብየ ዝም ብልም ጓደኛዬ አላስቻለውም አስተናጋጇን ድጋሚ ጠራት:: ደረሰኝ አምጭልን አላት:: ችግሩ ግን ቤቱ ደረሰኝ አልነበረውም:: ‹‹ደረሰኝ የለንም›› ስትል እኔም ነገሩ አላማረኝምና ‹‹እንዴት ይህን የሚያክል ቤት ያለ ደረሰኝ ይሠራል?›› አልኳት:: ምክንያቱ እሷም አልገባትም መሰለኝ ባለቤቱን ልጥራላችሁ አለችን:: እኛም ቢመጣም ምናልባት ተበላሽቶብን ነው ወይም አዲስ ስለሆንን ነው ከማለት ያለፈ ምንም አይለንም ብለን በቸልተኝነት ተይው ብለናት ወጣን::

አሁን ግን ሳስበው ግዴለሽ መሆናችን ልክ አልነበረም:: በእንዲህ አይነት ግዴለሽነት ነው ሕገ ወጥ አሠራሮች የሚለመዱት:: በተናጠልም ሆነ እንደ አገር ጉዳታቸው እየተለመደ ይሄዳል ማለት ነው:: የእንዲህ አይነት ትንንሽ ግዴለሽነቶች ናቸው ትልልቅ ጥፋቶችን የሚፈጥሩት::

አንድ ገጠመኝ ልጨምርና ወደ ጥቅል ትዝብቴ ልሂድ:: መገናኛ አንድ ካፌ ውስጥ ሦስት ሆነን የሚበላ ነገር አዝዘን በላን:: ሒሳቡን የከፈለው አንደኛው ልጅ ብቻ ስለሆነ ሁለታችን ሒሳቡንም መልሱንም ልብ አላልነውም:: የሰጣት የድፍን ሁለት ሁለት መቶ ብር ኖቶች ነበር:: መልሱ ውስጥ መቶ ብር መኖር ነበረበት:: ልጁ ከመቶ ብር በታች ያሉ የ10 ብር ኖቶችን ከመልስና ደረሰኝ ማምጫ ማህደሩ ውስጥ ካወጣ በኋላ መልሱ ልክ አለመሆኑ ገባው:: ወዲያውኑ ጠርቶ 100 ብር አስጨመራት::

ሊያጋጥም የሚችል ስህተት ነው በሚል ልብ አላልነውም ነበር፤ በኋላ ግን አብረውን የነበሩት ሁሉ እንዲህ አይነት ማጭበርበሮች የተለመዱ መሆናቸውን ገጠመኞቻቸውን እያነሱ ነገሩን:: ሰዎች መልስ ሲያነሱ ልብ አይሉትም በሚል ሆን ብለው ያደርጋሉ ይባላል:: የሁለት መቶ ብር ኖት ደግሞ ለዚህ መዘናጋት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል::

በእርግጥ ስህተት አያጋጥምም አይባልም፤ ሁላችንም እንሳሳታለን:: ዳሩ ግን ሆን ተብለው የሚደረጉ ካሉ ግን በቤቱ ውስጥ እምነት ማሳጣት ነው:: ለአስተናጋጆችም ቢሆን ጉርሻ ጭምር የሚያሳጣ ይሆናል:: መልሱን ልብ ሳይሉ ያነሱታል በሚል መጓጓት ውስጥ ከገቡ ችግር ነው፤ ምክንያቱም ልብ የሚል ደንበኛ ከተገኘ ተሳስታ ነው ብሎ በየዋህነት ከሚያስበው ይልቅ ሆን ብለው ለማጭበርበር ነው ብሎ የሚጠራጠረው ይበዛል:: ስለዚህ እዚህ ላይም ጥንቃቄ መደረግ አለበት::

ወደ ደረሰኞች እንሂድ:: በብዙ የአገልግሎት (ሰርቪስ) ቤቶች ‹‹ደረሰኝ ሳይቀበሉ ሒሳብ አይክፈሉ›› የሚሉ ማሳሰቢያዎችን በየግድግዳው ላይ እናያለን:: ሆኖም ግን ደረሰኝ ባይቀበሉም ሒሳብ ይክፈሉ እየሆነ ነው::

በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 19(3) መሠረት የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ማንኛውም ግብር ከፋይ ደረሰኝ እንዲሰጥ ይገደዳል:: ካለደረሰኝ ግብይት ካከናወነ የወንጀል ቅጣቱ በሕግ ተደንግጓል::

የግብር ከፋይነት ደረጃቸው ባይታወቅም፣ መቼም እነዚህ ካፌዎችና ሆቴሎች ግብር ከፋይ አይሆኑም ተብሎ አይገመትም:: በእርግጥ የግብር ከፋይነት ደረጃ የሚተመነው በቤቱ አይነትና ስም ሳይሆን በካፒታላቸው መጠን እንደሆነ ባለሙያዎች ይነገራሉ:: ምናልባት ደረሰኝ የማይሰጡ ቤቶች የደረጃ ሐ ግብር ከፋይ ከሆኑ ደረሰኝ ለመቁረጥ ላይገደዱ የሚችሉበት ሁኔታ አለ:: ዳሩ ግን የደረጃ ሐ ግብር ከፋይ ከሆነና ደረሰኝ ከሌለው ግን በዚያ ልክ የተጋነነ ዋጋ ሊያስከፍል አይገባውም:: ስለዚህ ገና ለገና ደረሰኝ የለንም ብለው ያጭበረብሩበታል ማለት ነው::

ተገልጋዩ የሚያየው የቤቱን ሁኔታ ብቻ ሊሆን ይችላል፤ በእርግጥ የሚሰጡት አገልግሎትም ጥሩ ሊሆን ይችላል:: ዳሩ ግን ከግብር ከፋዮች በላይ ማስከፈል ደግሞ ዝርፊያ ነው ማለት ነው:: ዋናው ችግር ግን ምናልባትም ደረሰኝ መቁረጥ የሚገባቸው ሆነው ማንም አስቦት ሊጠይቀን የሚችል የለም በሚል እያጭበረበሩበት ነው::

አንድ የንግድ ቤት ፈቃድ አውጥቶ ሥራ ሲጀምር መሟላት ያለባቸውን ሕጋዊ ሁኔታዎች አሟልቶ ነው:: ምናልባት ግዴለሽ ያልሆነ ሰው ቢያጋጥማቸው ሊቀጡ ወይም ንግድ ቤታቸው ሊዘጋባቸው ይችላል:: ስለዚህ ለትንሽ ማጭበርበር ብለው ትልቅ ኪሳራ ውስጥ ሊገቡ አይገባም:: ምናልባትም ሆን ብለው ለማጭበርበርም ላይሆን ይችላል፤ በግዴለሽነት ከሆነም፣ በተራ ግዴለሽነት ኪሳራ ላይ መውደቅ የለባቸውም::

ግዴለሽነት ብቻ ነው ብሎ ለመገመት ግን ይከብዳል:: ምክንያቱም የሚያስከፍሉት ሒሳብ ደግሞ የተጋነነ ነው:: የተጋነነ ሒሳብ ክፈል የተባለ ሰው ደግሞ ደረሰኝ መጠየቁ አይቀርም:: ምክንያቱም አስተማማኙ ደረሰኙ ነው:: ገና ለገና የኑሮ ውድነቱ በየዕለቱ ይጨምራል ተብሎ መሆን ካለበት በላይ መሆን የለበትም:: ደረሰኝ አለመቁረጣቸው ሳያንስ የተጋነነ ዋጋ ማስከፈላቸው እንደ ግለሰብም፣ እንደ ሀገርም እያከሰሩ ነው::

ብዙዎቻችን ሕጋዊ መብቶችን የመጠየቅ ችግር አለብን:: ይሉኝታ እንዳለ ሆኖ በብዛት ግን ግዴለሽነት ነው:: ከአገልግሎት ሰጪው ቤት ግድግዳ ላይ ‹‹ደረሰኝ ሳይቀበሉ አይክፈሉ›› የሚል ጽሑፍ እናያለን፤ ችግሩ ግን ጽሑፉን እንደማንኛውም የግድግዳ ላይ ጥቅስ እንጂ እንደ ሕጋዊ ግዴታ እያየነው አይደለም::

ለመሆኑ ግን አንድ ትልቅ ቤት ያለደረሰኝ የተጋነነ ሒሳብ የሚጠይቀው በምን ድፍረት ይሆን? ተገልጋዩ ዜጋ መብቱን የማይጠይቅ ግዴለሽ ነው በሚል መተማመን ይሆን ወይስ ቢጠይቅም የመጣው ይምጣ በሚል ይሆን?

ከዚሁ ከደረሰኝ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ካፌዎች የምታዘበው ነገር ደግሞ ደረሰኝ በእጅ ጽሑፍ የሚሠሩ አሉ:: ምክንያታቸው መብራት ጠፍቶ ነው የሚል ነው:: ችግሩ ግን ለማጭበርበር ስለሚያመች በተደጋጋሚ የሚጠቀሙትም እንዳሉ ነው ቅሬታ የሚነሳው:: ለማጭበርበር ብለው የሚያደርጉ ካሉ አንዱ ደፋር የጠየቃቸው ዕለት ጉድ ይፈላል:: ለምሳሌ፤ በዚያ አካባቢ መብራት አለመጥፋቱን ካወቀና መብራት ሳይጠፋ በእጅ ጽሑፍ ከቆረጡ የምርም እያጭበረበሩ ነው ማለት ነው::

በአጠቃላይ ሕጋዊ ግዴታዎችን የመጠየቅ ልምድ ይኑረን:: ይህን የምለው ራሴን ጭምር ተወቃሽ በማድረግ ነው:: እንደሀገር ያለውን ሁኔታ የሚቀይረው የግለሰቦች ጥረት ነውና ሕግ አክባሪም አስከባሪም እንሁን!

# ዓለም አቀፍ

## በናይጄሪያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ጠመንጃ ታጥቀው የሰበኩት ፓስተር መነጋገሪያ ሆኑ


ናይጀሪያዊው ፓስተር እሁድ ዕለት ክላሽንኮቭ ጠመንጃ ታጥቀው ስብከት ላይ መገኘታቸው በምዕመናኑ ዘንድ ግራ መጋባትን ሲፈጥሩ በሀገሪቱ ውስጥ መነጋገሪያ ሆነዋል።

በአቡጃ ከተማ ውስጥ በሚገኘው ‘ሐውስ ኦን ዘ ሮክ’ የተባለው ቤተክርስቲያን ሰባኪ የሆኑት ኡቼ አይግቤ፣ ትናንት እሁድ ለስብከት ወደ መድረክ የወጡት ኤኬ47 የተባለው ጠመንጃ አንግበው ነበር። በርካታ ምዕመን በታደመበት የፀሎት ሥነ ሥርዓት ላይ ፓስተሩ ጠመንጃ ታጥቀው ወደ መድረኩ ሲወጡ በርካቶች ግራ ተጋብተው የነበረ ሲሆን፣ ይህንን የሚያሳየው ቪዲዮም በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ በስፋት ታይቷል።

ፓስተሩ በትምህርታቸው ወቅት ጠመንጃ መታጠቃቸውን የምዕመናኑን “ልብ ከሐሰተኛ መምህራን ከመጠበቅ” እና “እምነት ያለ ሥራ ምንም መሆኑን” ለማሳየት ተጠቅመውበታል ተብሏል። ፓስተሩ ሐሰተኛ መምህራን ያሏቸውን በተመለከተ ድርጊታቸውን በስፋት ያብራሩ ሲሆን፣ “ስለዚህም የዕምነት መሣሪያችንን ታጥቀን መቆም ያለብን” ብለው በምሳሌ ለማስተማር ሞክረዋል።

“አንዳንዶች ችግር ይገጥመዋል ብለው እየጠበቁ ነው። እኔም ተዘጋጅቼ ነው የመጣሁት” በማለት ጠመንጃቸውን እያሳዩ መድረክ ላይ ቀልድ ጣል አድርገዋል። ፓስተሩ ከምዕመኑ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ስለሚሰበስቡ ሰባኪያን በማንሳት “ከእንዲህ ዓይነቶች እራሳችንን ለመጠበቅ መታጠቅ አለብን” በማለት ጠመንጃቸውን ለምሳሌው ተጠቅመውበታል።

በናይጀሪያ ሕግ መሠረት አንድ ሰው ሕጋዊ የጦር መሣሪያ መታጠቅ የሚችለው በፖሊስ ባለሥልጣን ፈቃድ ሲያገኝ ብቻ ነው። በርካቶችን ያነጋገረው የፓስተሩ መሣሪያ ታጥቆ ለስብከት መገኘት ሲሆን፣ በተጨማሪም ጠመንጃው የፓስተሩ ይሁን የሌላ ሰው እንዲሁም በመሣሪያው ውስጥ ጥይት ስለመኖሩ የታወቀ ነገር የለም።



በናይጀሪያም ሆነ በሌሎች ሀገራት ውስጥ የሃይማኖት መምህራን በሚሰብኩበት ጊዜ የጦር መሣሪያ አንግተው ወደ መድረክ መውጣት የተለመደ ነገር አይደለም። በዚህም ሳቢያ የፓስተር ኡቼ አይግቤ ድርጊትን የሚያሳየው ቪዲዮ በስፋት ከመሰራጨቱ ባሻገር በመላው ናይጀሪያ መነጋገሪያ ሆኗል።

የሰባኪውን ጠመንጃ ታጥቆ ወደ ቤተክርስቲያን መምጣትን በተመለከተ ፓስተሩ ሲሰብኩበት የነበረው ቤተክርስቲያ ማብራሪያ እንዲሰጥ ጥያቄ ቢቀርብለትም ምላሽ አልሰጠም። ጠመንጃ አንጋቹ ሰባኪ በመሩት የእሁድ ሥነ ሥርዓት ላይ የተከሰተ ችግር ስለመኖሩ እና የጦር መሣሪያውን በተመለከተ ከፖሊስም ሆነ ከሌሎች የመንግሥት ባለሥልጣናት የተባለ ነገር የለም ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## ቻይና የአሜሪካ በራሪ ፊኛዎች በተደጋጋሚ የአየር ክልሌን ጥሰዋል ብላ ከሰሰች

በአሜሪካ የአየር ክልል ሲንሳፈፉ ተገኙ በተባሉት ግዙፍ ፊኛዎች ምክንያት ውዝግብ ውስጥ የገቡት ቻይና እና አሜሪካ ሉዓላዊነትን በመጣስ እየተካሰሱ ነው። ባለፉት ቀናት በአየር ክልሏ ውስጥ ያገኘቻቸውን የቻይና ፊኛዎች በተዋጊ አውሮፕላኖች መትታ መጣሏን ያሳወቀችው አሜሪካ፣ ወደ ቻይና ተመሳሳይ ፊኛዎችን አሰማርታ እንደነበር ቻይና ገለጸች።

ውዝግቡ እየተባባሰ ባለበት በአሁኑ ወቅት የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዳስታወቀው ባለፈው የአውሮፓውያን ዓመት አሜሪካ ወደ ቻይና የአየር ክልል ከ10 ጊዜ በላይ ፊኛዎችን መላኳን ገልጿል። ቻይና ለአየር ሁኔታ ጥናት ያሰማራሁት ፊኛ ነው ያለችው እና አሜሪካ ግን ለስለላ የተላከ ነው ብላ የጠረጠረችውን ፊኛ ከሳምንት በፊት መትታ መጣሏ ይታወሳል።

ይህንንም ተከትሎ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለው ግንኙነት ተበላሽቶ የቆየ ሲሆን፣ ባለፉት ቀናትም ምንነታቸው ያልተለዩ ተጨማሪ በራሪ አካላትን አሜሪካ መትታ እንደጣላች አስታውቃለች።

በጉዳዩ ዙሪያ ቻይና ለቀረበላት ጥያቄ በሰጠችው ምላሽ፣ አሜሪካ በተመሳሳይ የአየር ክልሏን የሚጥስ ድርጊት በተደጋጋሚ መፈጸሟን ገልጿለች። “በአሜሪካ ጭምር የሚፈጸሙ በሕገ ወጥ ሁኔታ የሌሎች ሀገራትን የአየር ክልል የመጣስ ድርጊቶች ብዙም ያልተለመዱ አይደሉም” ሲሉ የቻይና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ዋንግ ዌንቢን ለጋዜጠኞች ተናግረዋል።

“ባለፈው ዓመት ብቻ፣ የአሜሪካ ፊኛዎች ከቻይና ባለሥልጣናት ምንም አይነት ፈቃድ ሳያገኙ ከአስር ጊዜ በላይ በሕገ ወጥ መንገድ በቻይና የአየር ክልል ላይ ተንሳፈዋል።”ጨምረውም “አሜሪካ ቻይናን በመክሰስ ስም ከማጥፋቷ በፊት ወደ ውስጧ በመመልከት፣ ከድርጊቱ እራሷን ማንጻት መጀመር አለባት” ሲሉ መክረዋል።



ይህ የአሜሪካ የአየር ክልል ጥሰት ባጋጠመበት ጊዜ ቻይና ምላሽ የሰጠችው “ኃላፊነት በተሞላበት እና ሙያዊ በሆነ መንገድ ነው” ብለዋል - ቃል አቀባዩ። “አሜሪካ ወደ ቻይና ግዛት በሕገ ወጥ ሁኔታ ስላስገባቻቸው በከፍተኛ ርቀት ላይ ስለሚጓዙ ፊኛዎች የበለጠ ለማወቅ ከፈለጋችሁ፣ የአሜሪካንን መንግሥት እንድትጠይቁ ነው የምመክራችሁ” ብለዋል።

ይህንን የቻይና ክስን በተመለከተ አሜሪካ እስካሁን ያለችው ነገር የለም። በአሜሪካ የአየር ክልል ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የቻይና ፊኛ ሲንሳፈፍ በመገኘቱ ምክንያት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ኃላፊው አንቶኒ ብሊንከን ወደ ቻይና ሊያደርጉት የነበረው ጉብኝት መሰረዛቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

# ባለውለታዎቻችን

## ካርልሄይንዝ በም -የኢትዮጵያ የምንጊዜም ባለውለታ

ማሕሌት አብዱል

በዓለም ላይ ዘር ፣ ቀለም፣ ዝና፣ ማንነት እና ቦታ ሳይገድባቸው ለሰዎች በጎ አድርገው ያለፉ ግለሰቦች ቁጥር በጣም ጥቂት ነው:: በተለይም ደግሞ ባሕር አቋርጠው፤ የራሳቸውን ሕይወት አደጋ ላይ ጥለው በምንም ለማይዛመዷቸው ችግረኛ ሰዎች እንደሻማ ቀልጠው የሚኖሩ ሰዎችን ማግኘት አዳጋች ነው:: በጣታችን አንድ ሁለት ብለን ከምንቆጥራቸውና የበጎነት ማሳያ ከሆኑ ምርጥ ግለሰቦች መካከል ደግሞ የሰዎች ለሰዎች የእርዳታ ድርጅት መሥራች ካርልሄይንዝ በም አንዱና ግንባር ቀደሙ ናቸው::

ኢትዮጵያና መላው ሕዝቦቿ የማይዘነጓቸው እኚህ የሃገር ባለውለታ እ.ኤ.አ መጋቢት 16 ቀን 1928 ዓ.ም ዳርምስታድ ጀርመን ውስጥ ከስመጥር የሙዚቃ አቀናባሪ ኦስትሪያዊ አባታቸው ዶክተር ካርል ሄይንዝ በም እና ከታዋቂ ድምፃዊት እናታቸው ቲያ ሊንህርድ ብቸኛ ልጅ ሆነው ተወለዱ።

ካርል ወደ እርዳታ ፊታቸውን ከማዞራቸው በፊት በአገራቸው ጀርመን እና ኦስትሪያ እጅግ ታዋቂ የፊልም ተዋናይ ነበሩ። 'ሲሲ'፣ 'ፎክስ ኤንድ ሂዝ ፍሬንድስ' ፣ 'ላ ፓሎማ'፣ 'ዘ ስቶው አዌይ' እና 'ካም ፍላይ ዊዝ ሚ'ን ጨምሮ፤ በአሜሪካ፣ በጀርመን፣ በኦስትሪያና በሌሎች አገሮች በተሠሩ 45 ያህል ፊልሞች ላይ በመተወን ችሎታቸውን ያስመሰከሩ ተዋናይ ነበሩ።

በካርል የሕይወት ዘመን አዲስ ምዕራፍ የተከፈተው እ.ኤ.አ በ1981 ዓ.ም ነበር:: በወቅቱ ተወዳጅ በነበረ የጀርመን ቴሌቪዥን ፕሮግራም «ቬተን ዳሽ» ላይ በመቅረብ በጀርመን፣ በኦስትሪያና በስዊዘርላንድ ፕሮግራሙን ከሚከታተሉ 18 ሚሊዮን ተመልካቾች ጋር ባልተለመደ ሁኔታ ተወራረዱ:: ካርል በቀኝ እጃቸው አንድ ዶች ማርክ (የጀርመን ገንዘብ) ይዘው «እንወራረድ፤ ይህንን የቴሌቪዥን ፕሮግራም ከምትከታተሉት 18 ሚሊዮን ተመልካቾች ውስጥ አንድ ሦስተኛችሁ እንኳን በአፍሪካ በድርቅና በረሃብ ለሚሰቃዩ ሕዝቦች የዕርዳታ እጃችሁን ለመዘርጋት ፈቃደኛ አይደላችሁም» በማለት ተናገሩ:: በውርርዱ ከተረቱ ራሳቸው ካርል የዕርዳታውን ገንዘብ ይዘው ወደ አፍሪካ በመሄድ ቢያንስ ለአንድ ዓመት ያህል የሰው ልጅ በረሃብ እንዳይሞት እንደሚታደጉ ቃል ገቡ:: ካርል በውርርዱ ባይሸነፉም፣ ቀድሞውኑ ውርርዱ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ስልት ነበረና የተሰበሰበውን 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን የጀርመን ማርክ ሆነ። ካርልም በዚህም ገንዘብ "ሰዎች ለሰዎች" (Menschen für Menschen) የተሰኘ ግብረሰናይ ድርጅታቸውን መሠረቱ።

ካርል የኢትዮጵያ ሥራቸውን እ.ኤ.አ በ1982 ዓ.ም በሐረርጌ ክፍለ ሀገር የኤረር ሸለቆ አካባቢ በጦርነት እና በረሃብ የተፈናቀሉትን ሁለት ሺ የሐዊ ጎሳ አባላትን በማቋቋም ነበር የጀመሩት:: በማስከተልም በ1980ዎቹ አጋማሽ በኢሉባቦር አካባቢ ለሠፈሩ መቶ ሺ ያህል ሰዎች ሰብዓዊ ድጋፍ አድርገዋል:: ይህን የበጎ አድራጎት ጥረት ወደ ተቀናጀ የገጠር ልማት በመቀየር ዛሬ የሰዎች ለሰዎች ድርጅት በበርካታ የአገሪቱ ክፍሎች 56 ሺ ካሬ ኪሎ ሜትር በሚሸፍን አካባቢ ላይ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል::

በሠላሳ ዓመቱ የልማት ጉዞ ከ5 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ በጤና፣ በንፁሕ የመጠጥ ውኃ፣ በግብርና እና የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ፣ በትምህርት፣ በመሠረተ ልማት፣ የሴቶችን አቅም በማጎልበት፣ በቤተሰብ ምጣኔ እና በኤች.አይ.ቪ ኤድስ ፕሮግራም ያለ አንዳች የሃይማኖት፣ የጎሳና ፖለቲካ ልዩነት ተጠቃሚ ሆኗል::

በዚህ ድርጅት አማካኝነት በመላ ሀገሪቱ 363 ትምህርት ቤቶች፣ ስምንት የማሠልጠኛ ተቋማት፣ ዘጠኝ መዋዕለ ሕፃናትና ከትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ደረጃ ዕውቅና የተሰጠው አንድ የቴክኒክ ኮሌጅ በመገንባት እና በቁሳቁስና በትምህርት መርጃ መሣሪያዎች በማሟላት ተማሪዎች ንፁሕ፣ ብሩህ፣ ምቹና የተሟላ የመማሪያ አካባቢ እንዲኖራቸው ተደርጓል:: 102 ሺ 117 ገበሬዎች በኢ-መደበኛ ክህሎት ሲሠለጥኑ፣ 279ሺ777 ጎልማሳች መሠረታዊ የማንበብ እና መጻፍ ትምህርት ተከታትለዋል:: በተጨማሪም 1ሺ329 ተማሪዎች በመደበኛው የቴክኒክና ሙያ ትምህርት በዲፕሎማና ዲግሪ ተመርቀው በቀሰሙት ዕውቀት ሀገራቸውን በማገልገል ላይ ይገኛሉ::




በገጠራቱ ኢትዮጵያ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ልጃገረዶችና ሴቶች በማለዳ እንሥራ ተሸክመው መማሠንን ለማስቀረት 1ሺ862 የውኃ ጉድጓዶችና ምንጮች ጎልብተዋል:: ከዚህም ባሻገር 70 የመስኖ ሥራዎችና 77 ውኃ ማጠራቀሚያዎች ተገንብተዋል::

ለምስኪኖች በጎነት ማድረግ የማይታክታቸው ካርል በጤናው ዘርፍ ለነፍሰ ጡሮች፣ ለእናቶችና ለሕፃናት ልዩ ትኩረት የሰጡ ሲሆን፣ ሦስት ሆስፒታሎች እና የጅማ ሆስፒታል ማሻሻያ፣ 37 ክሊኒኮች፣ 14 ጤና ጣቢያዎችና 49 የጤና ኬላዎች ተገንብተዋል:: 39 አምቡላንሶች ለተለያዩ ከተሞች በማቅረብ የአገር አቀፍ ጤና አገልግሎት ሽፋን ደረጃ እንዲያድግ ተደርጓል:: ለ52 ሺ 847 የዓይን ሕሙማን የሕክምና ዕርዳታ ተደርጓል:: በርካታ የሕክምና ባለሙያዎች የሥልጠና ዕድል አግኝተዋል:: ስለኤች. አይ.ቪ ኤድስ የግንዛቤ መድረኮች ተፈጥረዋል:: በበሽታው ለሚሰቃዩ ወገኖችና ለወላጅ አልባ ሕፃናት ድጋፍ ተደርጓል:: በርካታ ሴቶች የአጭርና ረጅም ጊዜ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል::

ልበ ሩህሩሁ ካርል የሴቶች ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እስካልተሻሻለ ድረስ ኢትዮጵያ ከድህነት እንደማትወጣ እርግጠኛ በመሆናቸው፣ የሴቶችን አቅም ለማጎልበትና የፆታ እኩልነት ለማስፈን 20 ሺ 351 ሴቶች በማኅበር ተደራጅተው ብድር በማግኘት ለሥራ ተሰማርተዋል:: እንዲሁም 60 ሺ 429 እማ ወራዎች በባልትና ፣ በቤት አያያዝ ፣ በግልና አካባቢ ንጽሕና ሠልጥነዋል:: በተጨማሪም 188 ሺ 738 ማገዶ ቆጣቢ ምርጥ ምድጃዎች እንዲሠራጩ ተደርጓል:: ንፁሕ የመጠጥ ውኃ በመንደራቸው አቅራቢያ በመገኘቱ የሴቶችን የሥራ ጫና እና ድካም የቀነሰ ሲሆን፣ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ የሚደረገው የተጠናከረ ዘመቻ መብታቸው እንዲከበር አስተዋጽኦ አበርክቷል::

ካርል በመሠረቱት በዚሁ ድርጅት አማካኝነት ተፈጥሮን በማያዛባ ሁኔታ የእርሻ ምርትንና ምርታማነትን ለማሳደግና በምግብ ራስን ለመቻል ለአነስተኛ ገበሬዎች ተገቢው የእርሻ ቴክኖሎጂ እና የመስኖ ዘዴ የማስተዋወቅ፣ ምርጥ ዘር የማቅረብና የአፈር እና ደን አጠባበቅ ሥልጠና ተሰጥቷል:: ከ150 ሚሊዮን ያህል ችግኞች ለገበሬዎች ተከፋፍለዋል::

ከዚህም ባሻገር 46 ሺ 702 ኪሎ ሜትር የድንጋይና አፈር፣ 4ሺ 068 ኪሎ ሜትር የቬቲቨር አፈር ጥበቃ እርከን፣ 18 ሺ 841 የተሻሻሉ መኖሪያ ቤቶች ተሠርተዋል:: የእንስሳትን ተዋፅዖ ለማሳደግ 30 የእንስሳት ሕክምና ጣቢያዎች ተገንብተዋል:: ለገበሬዎች የተሠራጩት 6 ሺ 228 ዘመናዊ ቀፎዎች አማራጭ የገቢ ምንጭ ፈጥረዋል:: እንዲሁም በገጠር መሠረተ ልማት ግንባታ ዘርፍ 2 ሺ 942 ኪሎ ሜትር መንገድና 15 ድልድዮች የተሠሩ ሲሆን፣ እንደ አብዲ ቦሪ የሕፃናት መንደር ያሉት ማኅበራዊ ተቋማት ወላጅ ለሌላቸው ሕፃናትና ወጣቶች የተሻለ የኑሮ አማራጭና የትምህርት ዕድል ፈጥረዋል::

የበጎነት አብነት የሆኑት ካርልሄይንዝ በም ለ33 ዓመታት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ላደረጉት ሰብዓዊ በጎ አድራጎትና የልማት አስተዋፅዖ ከተለያዩ የአውሮፓና የኢትዮጵያ ተቋማት ሽልማቶችና የክብር ማዕረጎች አግኝተዋል:: ከእነዚህ መካከል የኦስትሪያ የኤስል ማኅበራዊ ሽልማት(2011)፣ የስዊዘርላንድ ባልዛን ሽልማት (2007)፣ የጅማና ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲዎች የክብር ዶክትሬት(2003)፣ እንዲሁም ታላቁ የጀርመን ኦርደር ኦፍ ሜሪት(2001) ይጠቀሳሉ::

ካርል የላቀ ትርጉምና ስሜት የሚሰጣቸው ግን፣ በኢትዮጵያ መንግሥት የተሰጣቸው የክብር ዜግነት እንደሆነ መናገራቸው ይታወሳል:: ኢትዮጵያን እንደ አገራቸው፣ሕዝቧን እንደወገናቸው ሲቆጥሩ ለኖሩት ካርል፣ "ከእንግዲህ አንተ ባዕድ ሳትሆን ከእኛ እንደ አንዱ ነህ" ተብለው ሕልማቸው እውን የሆነበትን ቀን እጅግ ይደሰቱበታል::

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በበኩሉ አደባባይ በስማቸው የሰየመ ሲሆን፣ የሰዎች ለሰዎች ፕሮጀክቶች ተጠቃሚዎች ገንዘብ በማዋጣት የመታሰቢያ ሐውልታቸው እንዲቆም ተደርጓል:: በመርሐቤቴ ዓለም ከተማ ደግሞ ሐውልት ቆሞላቸዋል። እሳቸው ሐውልቱ በተመረቀበት እለት ለተሰጣቸው እውቅና እና ኢትዮጵያውያን ላሳያቸው ፍቅር «እኔ ፈረንጅ አይደለሁም ኢትዮጵያዊ እንጂ!» በማለት በስሜት ተናግረዋል::

ትናንት ካርል ባነፀው የሜንሸን ኮሌጅ የሠለጠኑ የጤና ሳይንስ ባለሙያዎች ብዙዎችን ኢትዮጵያውያን እናቶች ከምጥ ገላግለዋል፣ ብዙ የወደፊቱን ሀገር ተረካቢ ሕፃናትን አዋልደዋል:: የብዙዎችን ስቃይ አስታግሰው ወደ ፈውስ መልሰዋል:: ካርል አስተምሯቸው ያለፈው የኤሌክትሪካል ሣይንስ ባለሙያዎች ሀገራቸውን አገልግለዋል:: ካርል የመሠረተው ይህ ድርጅት ያስመረቃቸው የሜካኒካል ሳይንስ ባለሙያዎች ዛሬ በየተሽከርካሪው ኢንዱስትሪ፣ በየጋራዡ፣ በየፋብሪካው በብርቅ የሚፈለጉ ብቁ ሙያተኞች ሆነዋል:: ካርል የረዳቸው፣ ያስተማራቸው ሕፃናት ዛሬ አድገው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ፣ ሌሎችን የሚረዱ፣ የታነፀ ንፁሕ ዜጋ የሚያፈሩ ድንቅ ዜጎች ሆነዋል::

ካርል መኪናም ሆነ መንግሥት በማይዘልቃቸው ሩቅ ሩቅ የተረሱ የሀገሪቱ ክፍሎች ድረስ ሄዶ የሠራው ሆስፒታልና በየጫካው መሐል ምንም ነገር ሳያግዳቸው እንደ ትንግርት ደርሰው ለሕዝቡ ጤናን እያላበሱ ያሉ፣ ቢያንስ ቢያንስ የአንዲት ቀን ስቃዩን እያስታገሱ የቆዩ የእፎይታ ተቋማት ሆነዋል:: ካርል ከሁሉ ቀድሞ በከርቸሌ የሚገኙ እስረኞች በሜንሸን ፎር ሜንሸን ሠልጥነው የመስኖ እርሻ እንዲያለሙ፣ ለአካባቢያቸው ሕዝብ በዝቅተኛ ዋጋ እየሸጡ እንዲመግቡ፣ እና ከገቢውም ተጠቃሚ ሆነው በመታሰራቸው ኑሮ የጎደለባቸውን ቤተሰቦቻቸውን እንዲደግፉ፣ ለራሳቸው የማይደበዝዝ ዋጋ ያለው ሰውነት፣ ለቤተሰቦቻቸው የትም ይሁኑ የት በአለኝታነት የሚቆሙ ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጋ መሆናቸውን እንዲገነዘቡ በማድረግ ረገድም ያበረከተው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው::

መጠለያ የሚሆን ቤት በማጣታቸው ብቻ፣ የገንዘብ ዋስትና የሌላቸው ደሃ-አደግ በመሆናቸው ፣ መጠጊያ የሚሆናቸው ቤተሰብ ስለሌላቸው ብቻ ሀገራቸው ምን ደሃ ብትሆን በሜዳ ተበትነው እንዳይቀሩ፣ የባዕድነት ሥሜት በውስጣቸው ዘልቆ እንዳይጎዳቸው፣ ቅስማቸው እንዳይሰበር ካርል ብዙ ብዙ ሕፃናትን እና ወጣቶችን ከያሉበት ጥግ እየሰበሰበ በአዳሪ ትምህርት ቤት እያስገባ እስከ ኮሌጅ አስተምሯል::

ካርል በዚህ ድንቅ ሰብዓዊ ሥራው ጥቁር ነጭ አላለም፤ ዘር አልቆጠረም፤ ኦሮሞ አማራ ሰው አለየም:: ካርል በስህተት እንኳ የቆጠረው ዘር ቢኖር አንድ ብቻ ነው:: እርሱም ክቡሩ የሰው ልጅ ዘር ብቻ::

ካርል ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ ጊዜ ጀምሮ ከአልማዝ ተሾመ ጋር ትዳር መስርተው ልጆች ያፈሩ ሲሆን ጡረታ በወጡም ጊዜ የድርጅታቸውን አመራር ያስተላለፉት ለባለቤታቸው ለአልማዝ በም ነበር:: እኚህ ታላቅ ሰው በተለያዩ የኢትዮጵያ ገጠራማ ክልሎች የሠሯቸው ልማቶች እጅግ ሰፊ ናቸው።

በኢትዮጵያ በርካታ ሰብዓዊ ሥራዎችን በመሥራት ውለታን ከውለታም በላይ መሆን እንደሚችል ያሳዩት የሰው ለሰው ድርጅት መሥራቹ ካርል ሄንዝ በም ለረዥም ጊዜ በሕመም ሲሰቃዩ ቆይተው ግንቦት 21/2006 በጀርመን ሳልበርግ ሕይወታቸው ያለፈው::

በአንድ ወቅት በምድረ አውሮፓ ስመጥር የፊልም ተዋናይ ብቻ ሳይሆን ከሀብታም ቤተሰቦችም የወጣው ካርል ሄንዝ በም በሰውነት ሚዛን የላቀ እና ፍፁም ከወረደ ዘረኝነት የጸዳ፣ ጤናማ የሆነ የሰው ልጅ መልካም አስተሳሰብ ባለቤት መሆኑን ያለምንም ተጨማሪ ቃል ኢትዮጵያ ውስጥ ያሳለፈው ሕይወት ብቻውን ቁልጭ አድርጎ ይመሰክርለታል:: ታላቁ ይህ የኢትዮጵያውያን ወዳጅ በእነዚህ እና በሌሎች ተነግረው በማያልቁ ምክንያቶች የተነሣ ነው ዛሬም ሆነ ወደፊት ስሙ ከመቃብር በላይ ከፍ ብሎ ይታያል:: በሰብዓዊ መንፈሱና በማይሞቱ ሰብዓዊ ሥራዎቹ ገና ወደፊት ለትውልድም ካርልነቱን በተግባር እየተረጎመ፣ ብዙዎችን እያስተማረ፣ ብዙዎችን መልካምነት እያላበሰ፣ ዜጎቻችንን እያነፀ መኖሩን ይቀጥላል::

# ስፖርት





## ኢትዮጵያ በዓለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮና በጠንካራ ቡድን ትወከላለች

**ብርሃን ፈይሳ**

2022 የውድድር ዓመትን በስኬታማ ዓለም አቀፍ የውድድር ውጤቶች ያጠናቀቀው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ በቅርቡ የተያዘውን 2023 የውድድር ዓመትም በውጤት ለመጀመር ወጥኖ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ይህንንም በአውስትራሊያ ባትሪስ በሚካሄደው የዓለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮና ለመጀመር የቀናት ዕድሜ ብቻ ቀርተውታል።

የዘንድሮው የ44ኛው የዓለም ሃገር አቋራጭ ሻምፒዮና አዘጋጇ ከተማ ባትረስት እንግዶቿን መቀበል ጀምራለች። በመድረኩ በውጤታማነት የሚጠቀሰው የኢትዮጵያ ብሔራዊ አትሌቲክስ ቡድንም ወደ ስፍራው ከሚያቀኑት አንዱ ነው።

በወጣትና ምርጥ ብቃት ላይ በሚገኙ አትሌቶች የተገነባው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቡድን 28 አትሌቶችን እና 5 ተጠባባቂዎችን አካቶ ከትናንት በስቲያ ምሽት ወደ አውስትራሊያ ያቀና ሲሆን፤ በወጣት ወንድና ሴት፣ በአዋቂ ወንድና ሴት እንዲሁም በድብልቅ ሪሌ(ዱላ ቅብብል) የሚወዳደርም ይሆናል። ከጃንሜዳ ኢንተርናሽናል ሃገር አቋራጭ ውድድር በብቃታቸው ተመርጠው የተሰባሰቡ አትሌቶች ከጥር 3/2015 ዓም አንስቶ ዝግጅታቸውን በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፣ ጃንሜዳ፣ እንጦጦ፣ ሱሉልታ፣ ቃሊቲ፣ ወንጂና የተለያዩ አካባቢዎች በመዘዋወር ሲያከናውኑ ቆይተዋል። ቡድኑ በሥነምግባርና በስልጠና አቀባበሉ ምስጉን እንደነበረ የተገለጸ ሲሆን፣ በውድድሩ ላይ ስኬታማ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል። ይህ ስብስብ ያለው ጥንካሬም ለሌሎች ተፎካካሪ ሀገራት ፈተና እንደሚሆን የዓለም አትሌቲክስን ጨምሮ ትኩረታቸውን በአትሌቲክስ ላይ ያደረጉ ድረገጾች




**የአትሌቲክስ ብሔራዊ ቡድኑ በተሸኘበት ወቅት የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በአደራ ተረክባል ፤**

ከወዲሁ ቅድመ ግምታቸውን በማስቀመጥ ላይ ይገኛሉ።

ቡድኑ ወደ አውስትራሊያ ከማቅናቱ አስቀድሞ በተካሄደው የሽኝት መርሐ ግብር ላይም ብርቅዬ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች እንዳለፉት ጊዜያት የሃገራቸውን ስም በአሸናፊነት ያስጠሩ ዘንድ የአደራ ሰንደቅ ዓላማ ርክክብ ተከናውኗል። ይህንን ተከትሎም የሃገር አቋራጮች ውድድር ልዑኩን የሚመሩት የፌዴሬሽኑ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ወይዘሮ ሳራ ሐሰን፤ ቡድኑ ድልን አልሞ እንደሚጓዝ ገልጸዋል። የቡድኑ ዝግጅት መልካም ውጤት ሊመዘገብበት እንደሚችል የሚያመለክት መሆኑን የጠቆሙት ወይዘሮ ሣራ፤ በልምምድ ላይ የታየውን የቡድን ስሜት በማጠናከር አትሌቶቹ ለድል እንዲዘጋጁም አሳስበዋል።

የቀድሞዋ ድንቅ አትሌት የአሁኗ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ምክትል ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ፤ በሃገር አቋራጭ ሻምፒዮና የበርካታ ጊዜ ተሳትፎዋ ሦስት የወርቅ እና አንድ የብር ሜዳሊያዎችን ለሃገሯ ማስመዝገብ ችላለች። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰው ልጆች ሕይወት ስጋት በነበረው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ከአራት ዓመታት በኋላ ዘንድሮ ለ44ኛ ጊዜ የሚካሄደውን ውድድር አስመልክቶም ለቡድኑ የሥራ መመሪያ ሰጥታለች። በዚህም መሠረት በዝግጅት ወቅት ቡድኑ ያሳየውን መከባበርና መተባበር በውድድሩም በተግባር ማሳየት እንደሚገባው አሳስባለች።

በሽኝት መርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት በኢፌዴሪ ባሕልና ስፖርት ሚኒስትር የባህልና ቋንቋ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ወርቅነሽ ብሩ በበኩላቸው፤ የቡድኑ አባላት ከቀደሙ አትሌቶች ተምረው አሁንም የሃገራቸውን ስም ከፍ እንዲያደርጉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል። የኢፌዴሪ ባሕልና ስፖርት ሚኒስትር ከአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋር በመተባበር አትሌቶች በሄዱበት ውጤታማ እንዲሆኑ የሃገርን ስም በማስጠራት ባንዲራዋን እንዲያውለበልቡ ሲሠራ መቆየቱን አስታውሰዋል። በመሆኑም ቡድኑ ከዚህ ቀደም ከነበረው የተሻለ ውጤት አስመዝግቦ እንዲመለስ ተስፋ በመሰነቅ በጉጉት የሸኛቸው ሕዝብ በድል ሲመለሱም በሞቀ ሁኔታ አቀባበል እንደሚደረግላቸውም መልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል።

ከአራት ዓመት በፊት በዴንማርክ አህሩስ በተካሄደው የዓለም ሀገር አቋራጭ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ 2 የወርቅ፣ 3 የብር እና 2 የነሐስ በጥቅሉ 7 ሜዳሊያዎችን በማስመዝገብ ኬንያ እና ዩጋንዳን በማስከተል ቀዳሚ ሆና ማጠናቀቋ የሚታወስ ነው። ቻምፒዮናው ከተጀመረ አንስቶ በተካሄዱ 35 ተከታታይ ውድድሮች ላይ የተካፈለችው ኢትዮጵያ፣ 105 የወርቅ፣ 108 የብር እና 62 የነሐስ በድምሩ 275 ሜዳሊያዎችን ማግኘት ችላለች። ይኸውም ጎረቤት ሃገር ኬንያን ተከትላ በውድድሩ ታሪክ ከዓለም ሁለተኛ ደረጃ ላይ ልትቀመጥ ችላለች። ከእነዚህ ሜዳሊያዎች መካከል የሃገር አቋራጭ ንጉሱ አትሌት ቀነኒሳ በቀለ 6 ሜዳሊያዎችን በማግኘት ቀዳሚው ሲሆን፤ ፌዴሬሽኑን በዚህ ወቅት እየመራች ያለችው ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ እና ሌላኛዋ ምርጥ አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ ደግሞ ሶስት ሶስት ሜዳሊያዎችን በማስመዝገብ ይከተላሉ።

## አማራ ክልል

በከሳሽ ወ/ሮ ያየሽወርቅ ፈንታ እና በተከሳሽ አስፋው ትርፌ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክስ ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ የተከሰሱ መሆኑን በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው ለ27/6/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ ቀርበው እንዲከራከሩ ሲል የጎ/ሲ/እ/ወ/ፍ/ቤት አዟል፡፡

**በአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የጎንቻ ሲሶ እነሴ ወረዳ ፍርድ ቤት**

በአመልካች ወልዴ አድጎ እና በተጠሪዎች 1. አቶ ተስፋ አየነው ሞላ 2. መርጌታ በቃሉ አለማየሁ ጋረድ መካከል ስላለው የገንዘብ ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች የፍ/ቤቱን መጥሪያ ለመስጠት ቋሚ አድራሻ ያልተገኘ ወይም አድራሻቸው ውጪ አገር በመሆኑ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲጠሩ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ በሰጠው መሰረት ተከሳሾች ለቀጠሮው የካቲት 27 ቀን 2015 ዓ.ም ማዕ/ጎን/ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ቢሮ ቁጥር 08 በ4፡20 ሰዓት እንዲቀርቡ፤ ባይቀርቡ ግን ክርክሩ በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን ፍ/ቤቱ አዟል።

**በአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የማዕከላዊ ጎንደር ዞን ከፍ/ፍ/ቤት**

በከሳሽ ባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ እና ተከሳሽ 1. ዶ/ር ገነት ገ/ዮሐንስ 2. አቶ ዮሴፍ ገ/ዮሐንስ መካከል ስላለው የገንዘብ ክስ ክርክር ጉዳይ መከሰሳችሁን አውቃችሁ ክሱን በመዝገብ ቤት በኩል ወስዳችሁ መልሳችሁን ለ20/06/2015 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ በ3፡00 ሰዓት ባ/ዳርና አካ/ከፍ/ፍ/ቤት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባ/ዳርና አካ/ከፍ/ፍ/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ ወ/ሪት ራሄል ለገሰ እና በተከሳሽ ወ/ሪት ሚልዮን አለማየሁ መካከል ስላለው የፍ/ብሄር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ ወ/ሪት ሚልዮን አለማየሁ በተከሰሱበት ጉዳይ ለየካቲት 20 ቀን 2015 ዓ.ም 4፡30 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ እንዲቀርቡ ሲል በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ ችሎት አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች/ፍ/ባ/መብት 1ኛ አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ ኢ.ማ እና በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለዕዳ 1ኛ ኤሌክትሮ ላክስ ትሬዲንግ ኤንድ ኢንዱስትሪ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 3ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን አውቀው መልሱን በጽሑፍ በ10/6/2015 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት በ13/6/2015 ዓ.ም 4፡40 ሰዓት ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ን/ኢ ምድብ ችሎት**

አመልካች አቶ ሐይለ ይመር ተጠሪ ወ/ሮ መብራት ግደይ ከነሐሴ 2 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ የጠፉ ስለሆነ የመጥፋት ውሳኔ ይሰጥልኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ/ወ/ሮ መብራት ግደይ ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ለ10/6/2015 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ኮልፌ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ ወ/ሮ ረድኤት ግዛቸው መኮንን እና በተከሳሽ አቶ ደረጀ ተፈራ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ አቶ ደረጀ ተፈራ በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ ለ15/6/2015 ዓ.ም በ3፡00 ሰዓት ለሆነው ቀነ ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መናገሻ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ሲል ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ/አመልካች ወ/ሮ አለም ገዝሙ ወንዱ እና በተከሳሽ/ተጠሪ አቶ ፀሃዬ አረጋዊ መኮንን መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ /ተጠሪ በ20/06/2015 ዓ.ም. በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ አቶ ኢዮብ ሰለሞን እና በተከሳሽ ወ/ሮ ሰላማዊት ይትባረክ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ ወ/ሮ ሰላማዊት ይትባረክ ለ28/06/2015 ዓ.ም. በ3፡45 ሰዓት ለሆነው ቀነ ቀጠሮ ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መናገሻ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ/አመልካች ሕብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ ኢ.ማ እና በተከሳሽ/ተጠሪ 1ኛ አቶ ዛሂር ጀማል መሀመድ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ኛ ባ/ኢንሹራንስ ችሎት እየታየ መሆኑን አውቀው መልሱን በጽሁፍ ለ16/06/2015 ዓ.ም 5፡00 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት ለ20/06/2015 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ን/ኢ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች /ፍ/ባለመብት፡- 1ኛ ሕብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ ኢ.ማ እና በተከሳሽ/ተጠሪ/ፍ/ባለዕዳ፡- 1ኛ አቶ ችሎታው ጌታቸው ወንድማገኝ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 4ኛ ባ/ኢንሹራንስ ችሎት እየታየ መሆኑን አውቀው መልሱን በጽሁፍ ለ16/06/2015 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት በ20/06/2015 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ን/ኢ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች አቶ ሀብታሙ በላይ እና በተከሳሽ/በተጠሪ ወ/ሮ ህይወት ዴርሴማ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ተጠሪ/ተከሳሽ ወ/ሮ ህይወት ዴርሴማ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ችሎት ክስ የተመሰረተባቸው መሆኑን አውቀው በ22/06/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት በችሎት እንዲቀርቡ፤ የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ በሌሉበት የሚታይ መሆኑን አውቀው እንዲቀርቡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ችሎት አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**